# በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል መንግስት ጤና ቢሮ

## የ1998 በጀት አመት

## የጤናዉ ሴክተር አፈጻጸም ሪፖርት

ነሐሴ, 1998

ማውጫ

ገጽ

1. መግቢያ ........................................................................................ 2

2. የጤና ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ዘርፍ

2.1. ቤተሰብ ጤና ክብካቤ አገልግሎት ...................................................... ............ 3 - 19

2.1.2. ጤና ኤክስቴንሺን ፕሮግራም.......................................................................... 3

2.1.3. ክትባት አገልግሎት ......................................................................... 4- 13

2.1.4. ቤተሰብ ጤና ክብካቤ አገልግሎቶች ........................................................... 14 -19

2.2. ተላላፊ በሽታዎች መከላከልና ቁጥጥር................................................... ........ 20 - 28

2.2.1. ሳንባ ነቀርሳ፣ስጋደዌና አይነስዉርነት መከላከልና ቁጥጥር. .............................. 20 -24

2.2.2. ወባ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር......................................................... ............ 24 - 26

2.2.3. አካባቢ ጤና አገልግሎት......................................................................... . 27

2.2.4. የተቀናጀ የበሽታዎች ቅኝት ........................................................ ............ 27-28

2.3. መደበኛ ጤና አገልግሎት አቅርቦት....................................... .................. 29 -31

2.4. ጤና ተቋማት ማስፋፋትና ማጠናከር ......................................... ................ 31 -33

2.5. ሰው ኃይል ልማት........................................................ ............ .................. 34- 38

2.6. መድሀኒት አቅርቦትና አስተዳደር......................................... ....................... 38 - 40

2.7. ማኔጅመንትና የመረጃ ስርአት................................................................. 40

3.ኤች.አይ.ቪ/ኤድስመከላከያናመቆጣጠሪያዘርፍ................................................ 41- 51

አባሪዎች

# መግቢያ

የ1998 በጀት አመት የጤናው ሴክተር ዋና ተግባር የአምስት አመት የጤና ልማት መርሀግብር፣ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂና የምዕተ ዘመኑን የጤና ልማት ግቦች ለማሳካት ወሳኝ ስራዎች የተሰሩበት በጀት አመት ነው፡፡ በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አማካኝነት በሽታን ለመከላከልና ጤናን ለማጎልበት፣ እንዲሁም ኤች አይ ቪ/ኤድስ ተቋማዊና ማህበረሰባዊ ምላሽ ለመፍጠር የሚያስችል የሀሳብ፣ የአስተሳሰብና የአኗኗር ለዉጥ በምልአተ ህዝብ ደረጃ ለማምጣት የሚረዱ ተግባራትን ማከናወን፣ የጤና ልማት ሥራችን በሕዝብ ባለቤትነት እንዲፈጸም በበሽታ መከላከልና ጤና ማጐልበት ሥራችን ላይ ማነቆዎችን ለይቶ ማስተካከል፣ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራማችንን ሁሉን ደራሽና ሁሉን አቀፍ ማድረግ ፣ መሠረታዊ ጤና አገልግሎት ተቋማትን በተቀመጠላቸው የሕዝብ ሽፋን ስሌት ማዳረስ፣ የሠለጠነ የሰው ኃይል ፍላጐትን ለማሳካት መረባረብና የጤና አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር ስርዓት ማሻሻል ትኩረት የተሰጠባቸው ነበሩ፡፡

በጀት አመቱም ሴክተሩ በሁለት ም/ቢሮ ኃላፊዎች በሚመሩ የጤና ፕሮግራሞችና አገልግሎቶችና በኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጣሪያ ዘርፎች እንዲደራጅ በመደረጉ በሁለቱም ዘርፎች እቅድ አፈጻጸሙን በተመለከተ የቅርብ ድጋፍና ክትትል ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በጤና ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ዘርፍ የጤና ኤክስቴንሺን ፕሮግራም፣ የቤተሰብ ጤና ክብካቤ፣ የበሽታዎች መከላከያ፣ቁጥጥርና የተቀናጀ የበሽታዎች ቅኝትና የጤና አገልግሎትና የሰዉ ኃይል ልማት የተካተቱ ሲሆን የኤች አይቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዘርፍም በድጋፍና ክብካቤና በዘርፈ ብዙ ምላሽ መምሪያዎች ተደራጅተዉ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ፡፡ የሴክተሩም የ1998 በጀት ዓመት አፈጻጸም ዝርዝር ሪፖርት ሁለቱን ዘርፎች ባማከለ መልኩ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

# የጤና ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ዘርፍ

## ቤተሰብ ጤና ክብካቤ

### የጤና አገልግሎት ኤክስቴንሺን ፕሮግራም

የሕብረተሰባችን ንቃተ ጤና በማሳደግ ጤናማ ባህሪይ ፣ አኗኗር፣ አመጋገብና አስተሳሰብ መፍጠር ሕዝባችንን የጤናው ጉዳይ ባለቤት ከማድረግ ውጪ የማይፈጸም መሆኑ ቢታወቅም ይህንኑ ተቋማዊ አድርጎ መደገፍ የሚታለፍ አይደለም:: በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ *"ታሞ* **ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ"** የሚለውን አባባል ወደ ተግባር ያሸጋገርንበት የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራማችን በበጀት አመቱ አፈጻጸማችን ሙሉ በሙሉ የተሳካ ነበር:: ከ1997 ጀምሮ በድምሩ 2246 የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በእቅዳችን መሠረት ተመርቀው ወደየቀበሌያቱ እንዲመደቡ ተደርጓል:: ሠልጣኞች ከሴቶች ጉዳይ መዋቅር ጋር በመሆን የሁለት ሳምንት ማጠ ናከሪያ ሥልጠናና ተጨማሪ የሁለት ሳምንት የፖሊሲና ስትራቴጂዎች ሥልጠና ስለተሰጣቸው ከማንኛውም ጊዜ በላይ በሽታን የመከላከል ጤናን የማጐልበትና የሴክተሮች ትስስር ሁለንተናዊ ክህሎት እንዲኖራቸው ተደርጓል:: በ1998 በጀት አመትም 2228 አዲስ የኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በስድስት ማሠልጠኛ ተቋማት እንዲገቡ የተደረገ ሲሆን ከነዚህም ለመጀመሪያ ጊዜ ከቤንች ማጂና ደቡብ ኦሞ ዞኖች58 የአርብቶ አደር አካባቢ ሠልጣኞች በአርባ ምንጭ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ትምህርት ተከታትለዋል::

የከተማ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ተግባራዊ ማድረግ ይቻል ዘንድ ከፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ሲካሄድ የነበረው የመጨረሻው የጥናት ገጽታ እየተጠናቀቀ ሲሆን በ1999 በጀት አመት ወደ ተግባር የሚገባበት ይሆናል::

የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራማችንን ተቋማዊ ለማድረግ መሠረታዊ ጤና አገልግሎት ተቋማት ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ መሆኑ ይታወቃል:: ይህንንም እቅድ በህብረተሰብ ተሳትፎ እዉን ማድረግ ይቻል ዘንድ በ1997 እና በ1998 በጀት ዓመት ከ2272 በላይ ጤና ኬላዎች ግንባታ በመካሄድ ላይ ሲሆን በበጀት አመቱ በተደረገው ከፍተኛ ርብርብ 1374 ጤና ኬላዎች ተጠናቀዉ ለአገልግሎት ዝግጁ ሆነዋል:: የመከላከሉን የጤና አገልግሎት እያንዳንዱን ቤት ማኳኳት ይችል ዘንድ ይህንኑ መርህ በቅድሚያ አምነዉና ተግባራዊ ማድረግ ከጀመሩና በቀጣይም ጤናማ አኗኗርን ወደ ህብረተሰቡ ሰርጸ እንዲገባ የበኩላቸዉን አስተዋጽዎ ማበርከት በሚፈልጉ በጎ ፈቃደኛ የጤና መልእክተኖች መታጀብና መተግበር ያለበት መሆኑን በመታመኑ ይካዉ እንቅስቃሴ በበጀት አመቱም ተጠናክሮ ተካሂዷል:: አያሌ በጎፈቃደኛ የጤና መልእክተኞች ሰልጥነዉ በማገልገል ላይ ናቸዉ:: እስካሁንም ከ20 ሺህ በላይ ሰልጥነዋል::

የጤና ኤክስቴንሺን ፕሮግራሙ በቀጣይ ተጠናክሮ ይካሄድዘንድ በፕሮግራሙ ዙሪያ የሚታዩት፣ የባለሙያዎች ወደ ፈዉስ ህክምና የማድላት አዝማሚያዎች፣ በተመደቡበት ቀበሌያት በቋሚነት አለመኖር፣ የሚመሩበት እቅድና የስራ ፕሮግራም በቋሚነት አለመኖር ፣ የድጋፋዊ ክትትልና ለነሱ መሰጠት ያለበት ድጋፍ የተቀራረጠ መሆን እንዲሁም ወጥ የሪፖርት ማቅረቢና የእለት ተእለት ክንዉን መመዝገቢያ መዛግብት አለመኖር ችግሮች ሊሻሻሉ ይገባል::

## ክትባት

የሕፃናትንና የእናቶችን የሞት መጠን ለመቀነስ አንዱ መከላከያ ስልት ክትባት ፕሮግራምን ለሁሉም ተጠቃሚዎች ማድረስ መሆኑ ይታወቃል:: በበጀት አመቱም የቲቢ መከላከያ ክትባትን እድሜያቸዉ ከአንድ አመት በታች ለሆኑ ለ 615,780 ለመስጠት ታቅዶ አገልግሎቱን ለ544,853(88%) መስጠት ተችሏል:: ሽፋኑም በ1997 ከነበረበት 83% በ1998ወደ(84.6%) አድጓል::

የዘጊአናዳ -ትክትክ-መንጋጋ ቆልፍ/ዲፒቲ3/ ክትባትን በአመቱ ለ538,554 እድሜያቸው ከአንድ ዓመት በታች ለሆኑ ሕፃናት በመስጠት ሽፋኑን 95% ለማድረስ ታቅዶ በበጀት አመቱ አገልግሎቱን ለ 513,865 (95%) ተሰጥቷል:: ሽፋኑም 89% ተከናዉኗል:: የኩፍኝ መከላከያ ክትባትን እድሜያቸዉ ከአንድ አመት በታች ለሆኑ ለ510,209 ሕጻናት በመስጠት ሽፋኑን በ1997 ከነበረበት 82% ወደ 90% ለማሳደግ ታቅዶ በበጀት አመቱ አገልግሎቱ ለ 492,729 (96%) መስጠት ተችሏል:: ሽፋኑም ወደ 85.7% እድጓል::



በበጀት አመቱም እድሜያቸዉ ከ 1 አመት በታች ለሆኑ 479,926 ህጻናት የፖሊዮ ክትባት የተሰጠ ሲሆን ሽፋኑም 83.4% ደርሷል፡፡ በበጀት አመቱ ሁሉንም አይነት ክትባቶች ወስደዉ ያጠናቀቁ ህጻናት ቁጥር 360,317 ያህል ሲሆን ያጠናቀቁ ሽፋንም በ1997 59% ከነበረበት ወደ 62.67% አድጓል፡፡ የህጻናት ክትባት በተመለከተ በበጀት አመቱ በተደረገዉ ርብርብ በ1997 የደረስንበትን ግብ ለመጠበቅ መቻላችን የሚያበረታታ ቢሆንም ለአመቱ የተቀመጡት የዲፒቲ3፣የፖሊዮና ክትባት ያጠናቀቁ ህጻና ግብ ሙሉ በሙሉ አልተሳከም፡፡

የቴታነስ ወይም መንጋጋ ቆልፍ መከላከያ ክትባትን / TT2+ / ለ 476,119 እርጉዝ ለሆኑና 1,451,945 እርጉዝ ላልሆኑ ሴቶች ለመስጠት ታቅዶ በበጀት አመቱ ለ 438,365 (92%) እርጉዝ ለሆኑና 1,023,436 (70%) እርጉዝ ላልሆኑ ሴቶች ለመስጠት ተችሏል፡፡ የእርጉዝ ሴቶች የ TT2+ክትባት ሽፋን በ1997 መጨረሻ ከደረሰበት 61% ወደ 68 % የደረሰ ሲሆን እርጉዝ ያልሆኑ ሴቶች የ TT2+ክትባት ሽፋንም በ1997 መጨረሻ ደርሶበት በነበረዉ 35% በላይ ማሳደግ አልተቻለም፡፡ በበጀት አመቱም ተከታታይ የቴታነት መከላለያ ክትባት በዘመቻ መልክ በክልላችን ባሉ ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች ከአጋር ድርጅቶች ጋር በቅንጅት ተካሂዷል፡፡ በበጀት አመቱም በክትባት መረጃ አመዘጋገብና አያያዝ ዙሪያ የጥራት ጉድለት፣ በየተቋማቱ ያሉ የሪፖርት ፎርማቶችና ታሊሺቶች የተለያዩ መሆን ለዳታ ጥራት ተጠቃሽ ምክንያቶች በመሆናቸዉ ትኩረት ሰተን ማሻሻል ያለብን ጉዳዮች ናቸዉ፡፡ በሌላ በኩል የፖሊዮና የዲፒተ3ኀክትባት ሽፋን መለያየት ዘመቻን ተከትሎ የፖሊዮ ክትባት አለመሰጠቱን አመላካች መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ስለሆነም ይህም ክፍተት መሻሻል ይኖርበታል፡፡

**የስነምግብ ፕሮግራም**

በክልልላችን ለድርቅ ለተጋለጡ ዞኖችና ወረዳዎች መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በከፍተኛ የምግብ እጥረት የተጠቁ ( severe malnutrition) በአማካይ 1000 የጨቅላ ህፃናት በየወሩ ይታከማሉ ይህንኑ ችግር ከስሩ ለማቃለል ከዩኒሴፉና አደጋ መከላከል ጋር በመተባበር (Enhanced outreach እና Expanded EOS) በክልሉ በሙሉ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ በበጀት አመቱም በአመት ሁለት ጊዜ ማለትም በየ 6 ወሩ ከ 6 ወር እስከ 5ዓመት ለሆኑ ህጻናትቫይታሚን ኤ እደላ፣የሆድ ትላትል የማስወገድ (Deworming)- ከአንድ እስከ አምስት ዓመት ለሆኑ፣ደርሶ መልስ/ዉሎ ገብ የክትባት አገልግሎትን የማጠናከር ፣የጤና አጠባበት ትምህርት (Health education) በጤናና በሥነ ምግብላይ ሲካሄድ ቆይቷል፡፡

ለድርቅ ለተጋለጡ 55 ወረዳዎች የምግብ እጥረት ልየታ Screening for malnutrition ለህፃናትና ለእርጉዞች እንዲሁም ለሚያጠቡ እናቶች ተደርጎ መካከለኛ የምግብ እጥረት ( Moderate malnutrition) ላለባቸዉ ተጨማሪ ምግብ Supplementary food ከአደጋ መከላከልና ጋር በመተባበር ተሰቷል፡፡ እነዚህ ሥራዎች በአገራችን የምዕተ አመቱን የጤና ግቦች ለማሳካት

በ2015 የሕፃናትን ሞት በ63% ለመቀነስ በወጣው ዕቅድ ከ 30- 40% የሕፃናትን ሞት ሊቀነስ ይችላል ተብሎ ይገመታል፡፡ በበጀት አመቱም ENA (Essential nutrition action) ሥልጠና ለባለሙያዎች ተካሂዷል፡፡ ይህንኑ ለማስተባበር መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርድቶች በመተባበር child survival working group በክልል ደረጃ ተቋቁም በየወሩ እየተሰበሰበ በመሥራት ይገኛል፡፡

በ1998 በጀት አመት በታህሳስ ወር ለድርቅ ከተጋለጡ 54 ወረዳዎች 4ኛ ዙር EOS የተካሄደ ሲሆን በዚህም እንቅስቃሴ 1, 450, 406 ህጻናት የቫይታሚን ኤ እደላ ፣ አግኝተዋል፡ 87% ሽፋን ፡፡ የሆድ ጥገና ትላትል ማስወገድ (Deworming)- በተመለከተ 1,256,625 ከአንድ እስከ አምስት ዓመት የሆኑ ህጻናት መድሀኒት ተሰቷል ፡፡ ሽፋኑም 86% ደርሷል፡፡ በበጀት አመቱም እድሜያቸዉ ከ አምስት አመት በቻት የሆኑ 1,402,943 ተለክተዋል (Screening for malnutrition) ፣ 84% ሽፋንም ተከናዉኗል፡፡ 259788 እርጉዝ /ለሚያጠቡ እናቶች ተመሳሳይ የምግብ እጥረት ልየታ ስራ ተከናዉኗል ፡፡ በነዚሁ በድርቅ በተጋለጡ 54 ወረዳዎች በግንቦት ወር በተካሄደ የኩፍኝ መከላከያ ክትባት 1,328,450 ህጻናት ተከትበዋል 80% ሽፋን ተከናዊኗል፡፡ በበጀት አመቱ በቀሪዎቹ 50 ወረዳዎች 478984 የቫይታሚን ኤ ፣ 119867 የሆድ ጥገኛ ትላትል ማሰወደግ መድሀኒት ተሰቷል፣ ሽፋኑም እንደ ቅደም ተከተላቸዉ 76% % እና 74% ተከናዉኗል፡፡

**EOS activities performance**

| EOS round | De-worming Coverage | eligible children 6-59 months | Vitamin A supplement coverage | Lactating/pregnant Mothers with moderate malnutrition screened |
|---|---|---|---|---|
| 1st | 81% | 1,329,024 | 92% | 20% |
| 2nd | 83% | 1,329,024 | 93% | 19% |
| 3rd | 85% | 1381522 | 95% | 58% |
| 4th | 86% | 1,256,625 | 87% | 60% |

ሰንጠረዥ 1 ፡ **ከ1አመት በታች የቢሲጂ ክትባት የ1997 እና የ1998 አፈጻጸም በዞንና ልዩ ወረዳ**

| ተቁ | ዞን/ልወ | 1997 ክንዉን | | የ1998 ክንዉን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ቁጥር | ሽፋን (%) | ቁጥር | ሽፋን (%) |
| 1 | ቤ/ማጂ | 17,390 | 88.25 | 16,232 | 80.07% |
| 2 | ዳዉሮ | 11,355 | 70.53 | 13,830 | 83.61% |
| 3 | ጋሞጎፋ | 51,644 | 80.26 | 49,544 | 74.85% |
| 4 | ጌዲኦ | 29,913 | 88.19 | 30,930 | 88.56% |
| 5 | ጉራጌ | 49,184 | 73.21 | 46,876 | 67.85% |
| 6 | ሀዲያ | 49,327 | 86.67 | 56,090 | 95.84% |
| 7 | ካፋ | 19,880 | 57.45 | 26,874 | 75.52% |
| 8 | ከም/ጠ | 26,816 | 86.61 | 28,637 | 89.94% |
| 9 | ሸካ | 5,684 | 71.35 | 10,856 | 132% |
| 10 | ሲዳማ | 113,077 | 96.97 | 112,339 | 93.65% |
| 11 | ስልጤ | 27,714 | 81.71 | 31,713 | 90.98% |
| 12 | ደ/ኦሞ | 12,322 | 62.89 | 12,185 | 60.48% |
| 13 | ወላይታ | 63,862 | 92.09 | 68,323 | 95.79% |
| 14 | አላባ | 6,900 | 77.03 | 7,664 | 83.12% |
| 15 | አማሮ | 5,093 | 87.92 | 5,688 | 95.55% |
| 16 | ባሰኬቶ | 1,266 | 66.70 | 960 | 49.18% |
| 17 | ቡርጂ | 2,461 | 105.67 | 2,045 | 85.28% |
| 18 | ዲራሼ | 4,228 | 78.68 | 4,754 | 85.97% |
| 19 | ኮንሶ | 8,134 | 87.52 | 8,408 | 88.03% |
| 20 | ኮንታ | 3,131 | 86.92 | 2,312 | 62.44% |
| 21 | የም | 2,557 | 67.15 | 2,410 | 61.62% |
| 22 | አዋሳ ከተማ አስተ | 4,256 | 84.65 | 5,225 | 101.38% |
| | ክልል | 516,194 | 83.63 | 543,895 | 84.48% |

ሰንጠረዥ 2 : **ከ1አመት በታች የዲፒቲ3 ክትባት የ1997 አፈጻጸምና የ1998 እቅድ ክንዉን በዞንና ልዩ ወረዳ**

| ተቁ | ዞን/ልወ | 1997 ክንዉን | | 1998 እቅድ | 1998ክንዉን | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቁጥር | ሽፋን (%) | ሽፋን | ቁጥር | ሽፋን |
| 1 | ቤ/ማጂ | 15,310 | 87.00 | 91 | 14,437 | 80 |
| 2 | ዳዉሮ | 10,359 | 72.05 | 75 | 13,989 | 95 |
| 3 | ጋሞጎፋ | 42,253 | 73.53 | 77 | 42,810 | 72 |
| 4 | ጌዲኦ | 27,281 | 90.06 | 94 | 27,313 | 88 |
| 5 | ጉራጌ | 48,344 | 80.58 | 84 | 45,224 | 73 |
| 6 | ሀዲያ | 49,535 | 97.47 | 100 | 51,420 | 98 |
| 7 | ካፋ | 20,907 | 67.65 | 71 | 23,816 | 75 |
| 8 | ከም/ጠ | 24,668 | 89.22 | 93 | 26,764 | 97 |
| 9 | ሸካ | 5,743 | 80.73 | 84 | 10,784 | 125 |
| 10 | ሲዳማ | 116,741 | 112.11 | 100 | 111,913 | 104 |
| 11 | ስልጤ | 28,256 | 93.29 | 98 | 31,304 | 101 |
| 12 | ደ/ኦሞ | 10,874 | 62.15 | 65 | 12,030 | 67 |
| 13 | ወላይታ | 61,859 | 99.89 | 100 | 62,402 | 98 |
| 14 | አላባ | 6,956 | 86.96 | 91 | 7,187 | 87 |
| 15 | አማሮ | 5,407 | 104.52 | 100 | 5,047 | 95 |
| 16 | ባስኬቶ | 1,200 | 70.80 | 74 | 1,565 | 90 |
| 17 | ቡርጂ | 2,368 | 113.85 | 100 | 2,392 | 112 |
| 18 | ዲራሼ | 3,776 | 78.68 | 82 | 4,659 | 94 |
| 19 | ኮንሶ | 8,587 | 103.46 | 100 | 8,030 | 94 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 20 | ኮንታ | 3,081 | 95.77 | 100 | 2,212 | 67 |
| 21 | የም | 2,594 | 76.29 | 80 | 2,315 | 66 |
| 22 | አዋሳ | 4,246 | 94.57 | 99 | 5,296 | 115 |
| | ክልል | 500,345 | 90.77 | 95 | 513,865 | 89 |

ሰንጠረዥ 3 : **DPT1-DPT3 Dropout rate በዞንና ልዩ ወረዳ** 1998

| | | DPT1 | DPT3 | Drop out | |
|---|---|---|---|---|---|
| ተቁ | ዞን/ልወ | Achieved | Achieved | Number | Rate |
| 1 | ቤ/ማጂ | 18,226 | 14,437 | 3,789 | 20.79% |
| 2 | ዳውሮ | 14,883 | 13,989 | 894 | 6.01% |
| 3 | ጋሞጎፋ | 49,138 | 42,810 | 6,328 | 12.88% |
| 4 | ጌዲኦ | 31,511 | 27,313 | 4,198 | 13.32% |
| 5 | ጉራጌ | 47,790 | 45,224 | 2,566 | 5.37% |
| 6 | ሀዲያ | 55,508 | 51,420 | 4,088 | 7.36% |
| 7 | ካፋ | 28,636 | 23,816 | 4,820 | 16.83% |
| 8 | ከም/ጠ | 27,199 | 26,764 | 351 | 1.60% |
| 9 | ሸካ | 11,060 | 10,784 | 276 | 2.50% |
| 10 | ሲዳማ | 119,984 | 111,913 | 8,071 | 6.73% |
| 11 | ስልጤ | 32,752 | 31,304 | 1,448 | 4.42% |
| 12 | ደ/ኦሞ | 18,393 | 12,030 | 6,363 | 34.59% |
| 13 | ወላይታ | 65,536 | 62,402 | 3,134 | 4.78% |
| 14 | አላባ | 7,597 | 7,187 | 410 | 5.40% |
| 15 | አማሮ | 5,612 | 5,047 | 565 | 10.07% |
| 16 | ባስኬቶ | 1,729 | 1,565 | 164 | 9.49% |
| 17 | ቡርጂ | 2,280 | 2,392 | -112 | -4.91% |
| 18 | ዲራሼ | 5,642 | 4,659 | 983 | 17.42% |
| 19 | ኮንሶ | 8,755 | 8,030 | 725 | 8.28% |
| 20 | ኮንታ | 3,081 | 2,212 | 869 | 28.21% |
| 21 | የም | 2,472 | 2,315 | 157 | 6.35% |
| 22 | አዋሳከተማ | 5,238 | 5,296 | -58 | -1.11% |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ክልል | 563,022 | 512,909 | 50,029 | 8.87% |

ሰንጠረዥ 4 : **ከ1አመት በታች የፖሊዮ 3 ክትባት የ1997 እና የ1998 አፈጻጸም በዞንና ልዩ ወረዳ**

| ተቁ | ዞን/ልወ | 1997 ክንዉን | | የ1998 ክንዉን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ቁጥር | ሽፋን (%) | ቁጥር | ሽፋን (%) |
| 1 | ቤ/ማጂ | 12,471 | 70.87% | 12,204 | 67.41% |
| 2 | ዳዉሮ | 9,500 | 66.08% | 12,969 | 87.80% |
| 3 | ጋሞጎፋ | 39,983 | 69.58% | 41,055 | 69.46% |
| 4 | ጌዲኦ | 24,704 | 81.56% | 25,583 | 82.03% |
| 5 | ጉራጌ | 45,627 | 76.05% | 43,961 | 71.26% |
| 6 | ሀዲያ | 47,204 | 92.88% | 49,890 | 95.46% |
| 7 | ካፋ | 17,902 | 57.93% | 20,427 | 64.28% |
| 8 | ከም/ጠ | 23,532 | 85.12% | 27,073 | 95.22% |
| 9 | ሸካ | 5,382 | 75.65% | 9,169 | 106% |
| 10 | ሲዳማ | 109,583 | 105.23% | 107,233 | 100.11% |
| 11 | ስልጤ | 22,324 | 73.70% | 29,489 | 94.74% |
| 12 | ደ/ኦሞ | 9,162 | 52.37% | 9,868 | 54.85% |
| 13 | ወላይታ | 52,034 | 84.02% | 54,446 | 85.48% |
| 14 | አላባ | 6,201 | 77.52% | 7,156 | 86.92% |
| 15 | አማሮ | 4,814 | 93.06% | 4,898 | 92.14% |
| 16 | ባሰኬቶ | 1,057 | 62.36% | 1,455 | 83.48% |
| 17 | ቡርጂ | 2,262 | 108.75% | 2,361 | 110.28% |
| 18 | ዲራሼ | 3,213 | 66.95% | 3,726 | 75.46% |
| 19 | ኮንሶ | 5,652 | 68.10% | 7,920 | 92.86% |
| 20 | ኮንታ | 2,205 | 68.54% | 1,640 | 49.61% |
| 21 | የም | 2,529 | 74.38% | 2,171 | 62.17% |
| 22 | አዋሳ ከተማ አስተ | 4,234 | 94.30% | 5,232 | 113.69% |
| | ክልል | 451,575 | 81.92% | 479,926 | 83.47% |

ሰንጠረዥ 5 : **ከ1አመት በታች የኩፍኝ ክትባት የ1997 እና የ1998 አፈጻጸም በዞንና ልዩ ወረዳ**

| ተቁ | ዞን/ልወ | 1997 ክንዉን | | የ1998 ክንዉን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ቁጥር | ሽፋን (%) | ቁጥር | ሽፋን (%) |
| 1 | ቤ/ማጂ | 13,789 | 78% | 11,449 | 63 |
| 2 | ዳዉሮ | 10,322 | 71% | 13,804 | 93 |
| 3 | ጋሞጎፋ | 42,368 | 73% | 38,757 | 66 |
| 4 | ጌዲኦ | 22,698 | 74% | 22,545 | 72 |
| 5 | ጉራጌ | 43,864 | 73% | 41,652 | 68 |
| 6 | ሀዲያ | 45,173 | 88% | 55,310 | 106 |
| 7 | ካፋ | 19,258 | 62% | 20,690 | 65 |
| 8 | ከም/ጠ | 22,888 | 82% | 27,040 | 95 |
| 9 | ሸካ | 4,395 | 61% | 8,899 | 108 |
| 10 | ሲዳማ | 108,501 | 104% | 116,641 | 109 |
| 11 | ስልጤ | 25,603 | 84% | 28,494 | 92 |
| 12 | ደ/ኦሞ | 9,676 | 55% | 9,588 | 53 |
| 13 | ወላይታ | 56,244 | 90% | 62,787 | 99 |
| 14 | አላባ | 5,303 | 66% | 6,614 | 80 |
| 15 | አማሮ | 4,026 | 77% | 4,955 | 93 |
| 16 | ባሰኬቶ | 924 | 54% | 1,425 | 82 |
| 17 | ቡርጂ | 2,186 | 105% | 1,995 | 93 |
| 18 | ዲራሼ | 3,376 | 70% | 3,985 | 81 |
| 19 | ኮንሶ | 7,057 | 85% | 6,665 | 78 |
| 20 | ኮንታ | 2,543 | 79% | 2,183 | 66 |
| 21 | የም | 2,399 | 70% | 2,246 | 64 |
| 22 | አዋሳ ከተማ አስተ | 3,784 | 84% | 5,005 | 109 |
| | ክልል | 456,377 | 82% | 492,729 | 85 |

ሰንጠረዥ 6 : **ነፍሰጡር ለሆነ የቲቲ2 ክትባት የ1997 አፈጻጸምና የ1998 ክንዉን በዞንና ልዩ ወረዳ**

| ተቁ | ዞን/ልወ | 1997 ክንዉን | | 1998 ክንዉን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ቁጥር | ሽፋን (%) | ቁጥር | ሽፋን (%) |
| 1 | ቤ/ማጂ | 10,747 | 54.54 | 9,792 | 48.30% |
| 2 | ዳዉሮ | 6,369 | 39.56 | 7,004 | 42.34% |
| 3 | ጋሞጎፋ | 25,155 | 39.09 | 34,929 | 52.77% |
| 4 | ጌዲኦ | 20,075 | 59.18 | 20,710 | 59.30% |
| 5 | ጉራጌ | 42,806 | 63.72 | 41,905 | 60.66% |
| 6 | ሀዲያ | 49,773 | 87.46 | 56,609 | 96.73% |
| 7 | ካፋ | 12,104 | 34.98 | 13,742 | 38.62% |
| 8 | ከም/ጠ | 24,464 | 79.02 | 47,817 | 150.18% |
| 9 | ሸካ | 3,457 | 43.4 | 7,204 | 41.83% |
| 10 | ሲዳማ | 103,143 | 88.45 | 116,362 | 97.01% |
| 11 | ስልጤ | 26,026 | 76.73 | 26,247 | 75.30% |
| 12 | ደ/ኦሞ | 7,262 | 37.07 | 6,498 | 32.25% |
| 13 | ወላይታ | 28,462 | 41.04 | 27,169 | 38.09% |
| 14 | አላባ | 3,189 | 35.6 | 3,570 | 38.72% |
| 15 | አማሮ | 2,891 | 49.91 | 4,403 | 73.96% |
| 16 | ባሰኬቶ | 783 | 41.25 | 597 | 30.58% |
| 17 | ቡርጂ | 1,263 | 54.23 | 1,274 | 53.13% |
| 18 | ዲራሼ | 2,114 | 39.34 | 2,462 | 44.52% |
| 19 | ኮንሶ | 4,481 | 48.21 | 5,815 | 60.88% |
| 20 | ኮንታ | 1,083 | 30.07 | 437 | 11.80% |
| 21 | የም | 853 | 22.4 | 391 | 10.00% |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋሳ ከተማ አስተ | 2,227 | 44.29 | 3,428 | 66.51% |
| 22 | ክልል | 378,727 | 61 | 438,365 | 68 |

ሰንጠረዥ 7 : **ነፍሰጡር ላልሆኑ የቲቲ2 ክትባትየ1997 እና 1998 አፈጻጸም በዞንና ልዩ ወረዳ**

| ተቁ | ዞን/ልወ | 1997 ክንዉን | | 1998 ክንዉን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ቁጥር | ሽፋን (%) | ቁጥር | ሽፋን (%) |
| 1 | ቤ/ማጂ | 33,503 | 37.14 | 28,820 | 31.06% |
| 2 | ዳዉሮ | 33,637 | 45.64 | 28,022 | 37.01% |
| 3 | ጋሞጎፋ | 69,204 | 23.5 | 78,738 | 25.99% |
| 4 | ጌዲኦ | 31,752 | 20.45 | 33,216 | 20.78% |
| 5 | ጉራጌ | 173,584 | 56.44 | 142,231 | 44.98% |
| 6 | ሀዲያ | 69,213 | 26.57 | 83,137 | 31.03% |
| 7 | ካፋ | 42,023 | 26.53 | 46,081 | 28.29% |
| 8 | ከም/ጠ | 82,897 | 58.49 | 58,628 | 40.23% |
| 9 | ሸካ | 11,810 | 32.38 | 33,661 | 42.70% |
| 10 | ሲዳማ | 178,651 | 33.47 | 217,817 | 39.67% |
| 11 | ስልጤ | 68,670 | 44.23 | 62,433 | 39.13% |
| 12 | ደ/ኦሞ | 20,294 | 22.63 | 12,805 | 13.88% |
| 13 | ወላይታ | 139,792 | 44.04 | 140,361 | 42.99% |
| 14 | አላባ | 5,352 | 13.05 | 11,121 | 26.35% |
| 15 | አማሮ | 7,561 | 28.51 | 10,178 | 37.35% |
| 16 | ባሰኬቶ | 1,760 | 20.25 | 516 | 5.77% |
| 17 | ቡርጂ | 5,077 | 47.62 | 4,983 | 45.39% |
| 18 | ዲራሼ | 5,070 | 20.61 | 5,503 | 21.74% |
| 19 | ኮንሶ | 11,496 | 27.02 | 13,267 | 30.35% |
| 20 | ኮንታ | 6,932 | 42.04 | 2,682 | 15.82% |
| 21 | የም | 7,509 | 43.08 | 2,761 | 15.42% |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 22 | አዋሳ ከተማ አስተ | 2,855 | 12.04 | 6,475 | 27.45% |
| | ክልል | 1,008,642 | 35.7 | 1,023,436 | 34.73% |

**ቤተሰብ እቅድ አገልግሎት**

የቤተሰብ እቅድ አገልግሎትን በበጀት አመቱ ለ1,743,533 በመስጠት ሽፋኑን ወደ 60% ለማድረስ ታቅዶ አገልግሎቱን ለ1,658,114 ተጠቃሚዎች ለመስጠት ተችሏል፡፡ከእቅዱም (95%)ተከናዉኗል፡፡ ሽፋኑንም 56% ለማድረስ ተችሏል፡፡ ይሁንና በዚህ አገልግሎት ዘርፍ በተከታታይና ድጋሚ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች አመዘጋገብ ዙሪያ በባለሙያዎች መሀል እየታየ ያለዉ የዳታ አመዘጋገብ ልዩነትና የተጠቃሚዎች አመዘጋገብ ወጥነት የጎደለዉ/ ድግግሞሽ/ ና የተዘበራረቀ ሆኖ መታየት ለአፈጻጸም ክትትል ችግር እያስከተለ በመሆኑ ከወዲሁ እልባት ሊሰጠዉ ይገባል ፡፡




**ቅድመ ወሊድ ክብካቤ አገልግሎት**

በ1998 አገልግሎቱን ለ 444,378 ተጠቃሚዎች በመስጠት ሽፈኑን ወደ 70% ለማሳደግ ከታቀደዉ በበጀት አመቱ አገልግሎቱን ለ 393,780 (88%) ተጠቃሚዎች ተሰቷል። ሽፋኑም 61% ደርሷል። ይሁንና በበጀት አመቱ የተቀመጠዉን ግብ ለመድረስ አለመቻላችንን ፈትሸን የቀጣዩን አመት ግብ በተሳካ መልኩ ለማካሄድ ከወዲሁ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅብናል።




**ወሊድ አገልግሎት**

በ1998 መጨረሻ የወሊድ አገልግሎትን ለ 222,188 ወላዶች በመስጠት ሽፋኑን ወደ 35% ለማሳደግ ታቅዶ አገልግሎቱን መስጠት የተቻለዉ ለ163,162 ሲሆን ከእቅዱ 73% ተከናዉኗል። ሽፋኑም በ1997 ከነበረበት 18% ወደ 25% አድጓል። ይሁንና ለመድረስ የታቀዉ ግብ አልተደረሰም። በጤና ተቋማት የሚሰጠዉ የወሊድ አገልግሎት ከቀደምት አመታት ጋር ሲነጻጸር መሻሻል እየታየበት ቢሆንም የተጠቃሚዎች ቁጥር የሚፈለገዉን ያህል ያለመሆኑ የህብረተሰቡ ግንዛቤ ማነስ ብኣ ሳይሆን የሚሰጠዉ አገልገሎት የጥራት ችግር ያለበት መሆኑን ያመለክታል።



በበጀት አመቱ ሪፖርት ከተደረጉት 163,162 ወሊዶች 39%(63,319 ) ብቻ በጤና ተቋማት መሰጠቱ የኛ ጤና ተቋማት ምን ያህል ከህብረተሰቡ እንደራቁ አመላካች ነዉ ፡፡ ለዚህም ህብረተሰቡ በጤና ተቋማት የወሊድ አገልግሎት የሚጠቀምበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣ የህብረተሰቡ ንቃተ ጤና በማሳደግ በጤና ድርጅት ዉስጥ በሚሰጠዉ አገልግሎት ያለዉ እምነት እንዲጨምር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ህብረተሰቡ ለዚህም በእርግዝናና ከወሊድ ጋር ተያይዘዉ ለሚመጡ ድንገተኛ የጤና አገልግሎቶችን በቀረቤታ ሆነዉ አገልግሎት የሚሰጡ በቂ ጤና ተቋማትና በነዚሁ ተቋማት አገልግሎት የሚሰጡ በቂ ክህሎትና ዝግጁነት ያላቸወ ባለሙያዎች በየጤና ጣቢያዎች ላይ እንዲኖሩ ማደረግ አለማቻላችን ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸዉ፡፡ ይህንም ችግር ማቃለል ይቻል ዘንድ ከፌዴራል ጤና ጥበቃና ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመሆን መሰረታዊና አጠቃላይ ድንገተኛ የማዋለድ/ከጽንስ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ማቃለል የሚችሉ ተቋማትን የማጠናከር ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡፡፡ ከነዚህም ዉስጥ በክልሉ ባሉ ጤና ጣቢያዎችና ሆስፒታሎች የተጠናከረ የጤናማ እናትነት ፕሮግራም /የድንገተኛ የማዋለድ አገልግሎት መስጠት ይችሉ ዘንድ ባለሙያዎችን የማሰልጠንና ተቋማትን ለዚሁ አገልግሎት ብቁ በሚያደርጉ መሳሪያዎች የማሟላት እንቅስቃሴ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

እስካሁን በተደረገዉ ጥረት በክልሉ ካሉ 18 ሆስፒታሎች የግሉን ጨምሮ 15 አጠቃላይ የድንገተኛ የጽንስ/የማዋለድ አገልግሎት ( Comprehensive Emergency Care ) ይሰጣሉ፡፡ ጤና ጣቢያዎችም በተቻለ አቅም መሰረታዊ ድንገተኛ የጽንስ/ማዋለድ አገልግሎት( Basic Emergency Care ) መስጠት ይችሉ ዘንድ ድጋፍ እየተደረገላቸዉ ይገኛሉ፡፡ እስካሁን ባለዉ ሂደት በክልሉ ካሉ 154 ጤና ጣቢያዎች 8 ይህን አገልግሎት እንዲሰጡ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በክልላችንና በአገራችን ካለዉ ከፍተኛ የእናቶች ሞት አንጻር በሁለቱም አገልግሎት አይነቶች ገና ብዙ ይቀራል፡፡

ሰንጠረዥ 8 : **ቤተሰብ እቅድ የ1997 አፈጻጸምና የ1998 እቅድ ክንዉን በዞንና ልዩ ወረዳ**

| ተቁ | ዞን/ልወ | 1997 ክንዉን | | 1998 እቅድ | 1998 ክንዉን | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቁጥር | ሽፋን (%) | ሽፋን (%) | ቁጥር | ሽፋን |
| 1 | ቤ/ማጂ | 35,606 | 39.47 | 50 | 49,088 | 53 |
| 2 | ዳዉሮ | 22,448 | 30.46 | 39 | 29,673 | 39 |
| 3 | ጋሞጎፋ | 83,838 | 28.46 | 36 | 112,583 | 37 |
| 4 | ጌዲኦ | 60,348 | 38.87 | 49 | 97,776 | 61 |
| 5 | ጉራጌ | 157,475 | 51.21 | 65 | 203,023 | 64 |
| 6 | ሀዲያ | 181,034 | 69.49 | 88 | 204,680 | 76 |
| 7 | ካፋ | 78,670 | 49.66 | 65 | 82,614 | 50 |
| 8 | ከም/ጠ | 67,407 | 47.56 | 60 | 52,230 | 35 |
| 9 | ሸካ | 23,134 | 63.44 | 80 | 37,046 | 98 |
| 10 | ሲዳማ | 285,733 | 53.53 | 68 | 387,506 | 70 |
| 11 | ስልጤ | 99,639 | 64.17 | 81 | 119,577 | 74 |
| 12 | ደ/ኦሞ | 14,824 | 16.53 | 21 | 15,895 | 17 |
| 13 | ወላይታ | 132,934 | 41.88 | 53 | 187,123 | 57 |
| 14 | አላባ | 37,852 | 92.31 | 90 | 9,775 | 23 |
| 15 | አማሮ | 5,890 | 22.21 | 28 | 7,522 | 27 |
| 16 | ባስኬቶ | 4,591 | 52.83 | 67 | 4,112 | 46 |
| 17 | ቡርጂ | 3,477 | 32.61 | 41 | 2,698 | 24 |
| 18 | ዲራሼ | 6,230 | 25.33 | 32 | 7,090 | 28 |
| 19 | ኮንሶ | 6,286 | 14.77 | 19 | 16,920 | 38 |
| 20 | ኮንታ | 3,406 | 20.65 | 26 | 2,771 | 16 |
| 21 | የም | 4,363 | 25.03 | 32 | 4,797 | 26 |
| 22 | አዋሳአስተ | 24,039 | 104.44 | 90 | 23,615 | 100 |
| | ክልል | 1,339,224 | 47.4 | 60 | 1,658,114 | 56 |

ሰንጠረዥ 9 ፡ **እርግዝና ክትትል አገልግሎት የ1997 አፈጻጸምና የ1998 እቅድ ክንዉን በዞንና ልዩ ወረዳ**

| ተቁ | ዞን/ልወ | 1997 ክንዉን | | 1998 እቅድ | 1998 ክንዉን | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቁጥር | ሽፋን (%) | ሽፋን (%) | ቁጥር | ሽፋን |
| 1 | ቤ/ማጂ | 11,611 | 59.92 | 68 | 12,049 | 59.43% |
| 2 | ዳዉሮ | 6,533 | 40.58 | 47 | 7,367 | 44.54% |
| 3 | ጋሞጎፋ | 28,314 | 44 | 51 | 25,886 | 39.11% |
| 4 | ጌዲኦ | 16,124 | 47.54 | 55 | 17,863 | 51.15% |
| 5 | ጉራጌ | 51,481 | 76.63 | 88 | 45,665 | 66.10% |
| 6 | ሀዲያ | 40,227 | 70.68 | 81 | 41,409 | 70.75% |
| 7 | ካፋ | 15,837 | 45.76 | 53 | 16,930 | 47.58% |
| 8 | ከም/ጠ | 17,927 | 57.9 | 67 | 22,032 | 69.2% |
| 9 | ሸካ | 5,668 | 71.15 | 82 | 9,644 | 76.00% |
| 10 | ሲዳማ | 80,616 | 69.13 | 80 | 81,775 | 68.17% |
| 11 | ስልጤ | 20,955 | 61.78 | 71 | 21,506 | 61.70% |
| 12 | ደ/ኦሞ | 9,264 | 47.28 | 55 | 9,257 | 45.95% |
| 13 | ወላይታ | 39,788 | 57.37 | 66 | 50,184 | 70.36% |
| 14 | አላባ | 4,381 | 48.91 | 56 | 4,187 | 45.41% |
| 15 | አማሮ | 2,831 | 48.87 | 56 | 3,307 | 55.55% |
| 16 | ባስኬቶ | 771 | 40.62 | 47 | 1,162 | 59.53% |
| 17 | ቡርጂ | 2,247 | 96.48 | 70 | 1,462 | 60.97% |
| 18 | ዲራሼ | 4,340 | 80.76 | 93 | 4,944 | 89.40% |
| 19 | ኮንሶ | 7,930 | 85.32 | 98 | 9,058 | 94.84% |
| 20 | ኮንታ | 1,382 | 38.37 | 44 | 940 | 25.38% |
| 21 | የም | 1,458 | 38.29 | 44 | 1,168 | 29.86% |
| 22 | አዋሳ ከተማ አስተ | 5,967 | 118.68 | 100 | 5,971 | 115.85% |
| | ክልል | 375,652 | 60.86 | 70 | 393,780 | 61.16% |

ሰንጠረዥ 10 : **የወሊድ አገልግሎት የ1997 አፈጻጸምና የ1998 እቅድ ክንዉን በዞንና ልዩ ወረዳ**

| ተቁ | ዞን/ልወ | 1997 ክንዉን | | 1998 እቅድ | 1998 ክንዉን | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቁጥር | ሽፋን (%) | ሽፋን (%) | ቁጥር | ሽፋን |
| 1 | ቤ/ማጂ | 2,675 | 13.58 | 30 | 4,222 | 20.83% |
| 2 | ዳዉሮ | 1,273 | 7.91 | 15 | 1,876 | 11.34% |
| 3 | ጋሞጎፋ | 9,421 | 14.64 | 29 | 12,442 | 18.80% |
| 4 | ጌዲኦ | 4,128 | 12.17 | 23 | 5,328 | 15.26% |
| 5 | ጉራጌ | 23,008 | 34.25 | 65 | 24,280 | 35.15% |
| 6 | ሀዲያ | 6,583 | 11.57 | 23 | 10,700 | 18.28% |
| 7 | ካፋ | 3,152 | 9.11 | 18 | 4,376 | 12.30% |
| 8 | ከም/ጠ | 7,867 | 25.41 | 48 | 10,311 | 32.38% |
| 9 | ሸካ | 535 | 6.72 | 12 | 2,329 | 28% |
| 10 | ሲዳማ | 29,903 | 25.64 | 49 | 42,337 | 35.30% |
| 11 | ስልጤ | 6,517 | 19.21 | 36 | 9,445 | 27.10% |
| 12 | ደ/ኦሞ | 2,369 | 12.09 | 27 | 3,516 | 17.45% |
| 13 | ወላይታ | 6,654 | 9.59 | 20 | 18,965 | 26.59% |
| 14 | አላባ | 557 | 6.22 | 13 | 2,633 | 28.56% |
| 15 | አማሮ | 981 | 16.93 | 23 | 1,333 | 22.39% |
| 16 | ባስኬቶ | 33 | 1.74 | 3 | 264 | 13.52% |
| 17 | ቡርጂ | 668 | 28.68 | 53 | 1,155 | 48.17% |
| 18 | ዲራሼ | 774 | 14.4 | 32 | 1,555 | 28.12% |
| 19 | ኮንሶ | 1,688 | 18.16 | 34 | 3,604 | 37.73% |
| 20 | ኮንታ | 231 | 6.41 | 12 | 313 | 8.45% |
| 21 | የም | 732 | 19.22 | 36 | 871 | 22.27% |
| 22 | አዋሳ አስተ | 1,732 | 34.45 | 64 | 1,294 | 25.11% |
| | ክልል | 111,481 | 18.06 | 35 | 163,162 | 25.34% |

የሳንባ ነቀርሳ በሽታ፣ ስጋ ደዌና አይነስዉርነት  መከላከልና ቁጥጥር

በበጀት አመቱ የሳንባ ነቀርሳ መከላከያና ቁጥጥር ፕሮግራምን በስሩት ለማካሄድ በተደረገዉ ርብርብ የሳንባ በሽታ ህክምና አገልግሎትን በጤና ጣቢያ፣ ታዳጊ ጤና ጣቢያና  በሆስፒታል ደረጃ ሽፋኑን በ19997 ከነበረበት 99%  ወደ 99.5%  አድጓል።




የዶትስ ህክምና የሚሰጡ ጤና ኬላዎች ቁጥርም በ1997 ከነበረበት 127 በ1998 መጨረሻ ወደ 151 ከፍ ብሏል። ይሁንና ጤና ኬላ በስሌት ዉስጥ ሲገባ የክልሉን የጤና ተቋም ዶትስ ሽፋንን ዝቅ ያደርገዋል ። በሆስፒታል፣ በጤና ጣቢያ፣በታዳጊ ጤና ጣቢያና በጤና ኬላዎች ጭምር ሲሰላ ወደ 60%  ዝቅ ይላል። ይህም የሚያመለክተዉ ከክለሉ ህዝብ ዉስጥ 40%  የሚሆነዉ አገልግሎቱን ማግኘት አለመቻሉን ነዉ ። የሳንባ ነቀርሳ ህሙማን ልየታ በተመለከተ  በአክታቸዉ ተዋሱን ከሚያስተላልፉት 47% አግኝቶ ለማከም ተችሏል። ይህ ሽፋን የተሰላዉ የክልሉን የጤና ሽፋን መሰረት በማድረግ ነዉ። የሳንባ በሽታ ህክምና ስኬትን በተመለከተ በበጀት አመቱበ1997 መጨረሻ ከነበረበት  84% ወደ 85% ለማሳደግ የተቀመጠዉ ግብ ሙሉ በሙሉ ለመድረስ ተችሏል። በበጀት ዓመቱ 22,000 የሳንባ ነቀርሳ ሕሙማንን ለለመዝገብና ለማከም ከታቀደው 20231 (92%) ሕሙማንን ለመመዝገብና ለመከታተል ተችሏል። ከ1997 ዓመት ሕክምና ከጀመሩት 8422 የሳንባ ነቀርሳ ሕሙማን ዉስጥ 7138 (85%) የዳኑና የጨረሱ መሆናቸዉ ሪፖርት ተደርግዋል።

የቲቢና የኤች አይ ቪ ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ ለመጀመሪያዉ ፌዝ በክልሉ ዉስጥ ካሉ ጠ ና ተቋማት አገልግሎቱን በ45 ጤና ድርጅቶች ማስጀመር ይቻል ዘንድ በቲቢ ህክምና ክፍል ለሚሰሩ 45 ባለሙያዎች ስልጠና ከተሰጠ በኋላ አገልግሎቱን መስጠት ተጀምሯል። ምንም እንኳን ከሁሉም ጤና ድርጅቶች የተሟላ ሪፖርት ባይደርስም እስካሁን ባለን መረጃ ከ1 ሆስፒታልና 11 ጤና ጣቢያዎች 236 ( 128 ወንድና 108 ሴት) የቲቢ ህመምተኖች የኤች አይ ቪ ኤድስ የምክር አገልግሎት አግኝተዋል። የምክር አገልግሎት ካገኙ የቲቢ ህሙማን 157 (86 ወንድና 71 ሴት) የኤች አይ ቪ ኤድስ ምርመራ ተደርጎላቸዋል። ምርመራ ከተደረገላቸዉ ዉስጥ 51 (23 ወንድና 28 ሴት) ወይም 32% በደማቸዉ ቫይረሱ ተገቶባቸዋል።

ሰንጠረዥ 11 : **TB Case Detection Rate by Zone & Special Woreda, EFY 1998 E.C SNNP**

| No | zones or special woreda | population | TB cases Expected (0.356% of PoPn) | TB cases reported | Case Detection rate (All forms) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Alaba | 216439 | 771 | 218 | 28 |
| 2 | Amaro | 139743 | 497 | 176 | 35 |
| 3 | Awassa Town | 131012 | 466 | 810 | 174 |
| 4 | Baskato | 45836 | 163 | 41 | 25 |
| 5 | Bench Maji | 475902 | 1694 | 1093 | 65 |
| 6 | Burji | 56299 | 200 | 40 | 20 |
| 7 | Dawro | 388291 | 1382 | 376 | 27 |
| 8 | Derashe | 129818 | 462 | 86 | 19 |
| 9 | Gamo Gofa | 1553745 | 5531 | 1573 | 28 |
| 10 | Gedeo | 819873 | 2919 | 1606 | 55 |
| 11 | Gurage | 1621670 | 5773 | 2441 | 42 |
| 12 | Hadiya | 1373841 | 4891 | 2507 | 51 |
| 13 | Keffa | 835294 | 2974 | 645 | 22 |
| 14 | Kembata Tembro | 747397 | 2661 | 1183 | 44 |
| 15 | Konso | 224208 | 798 | 111 | 14 |
| 16 | Konta | 86927 | 309 | 59 | 19 |
| 17 | Sheka | 192655 | 686 | 325 | 47 |
| 18 | Sidama | 2805731 | 9988 | 3316 | 33 |
| 19 | Selite | 818257 | 2913 | 1225 | 42 |
| 20 | South Omo | 472977 | 1684 | 330 | 20 |
| 21 | Wolayita | 1674264 | 5960 | 2007 | 34 |
| 22 | Yem | 91821 | 327 | 63 | 19 |
| Total | Region | 14,902,000 | 53051 | 20231 | 38 |

## ሰንጠረዥ 12 : **Treatment out come of Smear Positive PTB case registered for treatment in 1997 E.C by zones and special woredas, EFY 1998 SNNPR**

| S.no | zones or special woreda | Treatment Success Rate % | Death Rate | Failure Rate | Defaulter rate | Transferred out rate |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | % | % | % | % |
| 1 | Alaba | 86 | 8 | 0 | 4 | 2 |
| 2 | Amaro | 90 | 2 | 0 | 3 | 5 |
| 3 | Awassa Town | 74 | 3 | 0 | 11 | 11 |
| 4 | Baskato | 75 | 4 | 0 | 14 | 7 |
| 5 | Bench Maji | 93 | 2 | 1 | 2 | 2 |
| 6 | Burji | 94 | 6 | 0 | 0 | 0 |
| 7 | Dawro | 97 | 3 | 0 | 0 | 0 |
| 8 | Derashe | 38 | 12 | 0 | 4 | 46 |
| 9 | Gamo Gofa | 82 | 3 | 0 | 9 | 6 |
| 10 | Gedeo | 83 | 4 | 0 | 9 | 4 |
| 11 | Gurage | 85 | 4 | 0 | 5 | 6 |
| 12 | Hadiya | 83 | 2 | 0 | 6 | 8 |
| 13 | Keffa | 50 | 5 | 0 | 6 | 14 |
| 14 | Kembata Tembro | 90 | 4 | 1 | 1 | 5 |
| 15 | Konso | 93 | 4 | 2 | 11 | 0 |
| 16 | Konta | 76 | 5 | 0 | 16 | 0 |
| | Sheka | 92 | 0 | 0 | 0 | 9 |
| 17 | Sidama | 88 | 3 | 0 | 7 | 2 |
| 18 | Selite | 92 | 4 | 0 | 1 | 3 |
| 19 | South Omo | 79 | 6 | 1 | 6 | 7 |
| 20 | Wolayita | 90 | 5 | 0 | 2 | 4 |
| 21 | Yem | 77 | 7 | 0 | 13 | 3 |
| Total | Region | 85 | 4 | 0 | 6 | 5 |

ሰንጠረዥ 13 : **Sputum conversion rate for smear positive cases registered during 4th quarter of 1997, 1st, 2nd and 3rd quarter of 1998 E.C SNNPR**

| Zone | New S.Po | Positive | % | Negative | % | Not done | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Alaba | 104 | 2 | 2 | 94 | 90 | 8 | 8 |
| Amaro | 113 | 2 | 2 | 87 | 77 | 24 | 21 |
| AwassaTown | 243 | 21 | 9 | 196 | 81 | 26 | 11 |
| Basketo | 20 | 0 | 0 | 10 | 50 | 12 | 60 |
| Bench Maji | 400 | 2 | 1 | 321 | 80 | 77 | 19 |
| Burji | 12 | 0 | 0 | 3 | 25 | 3 | 25 |
| Dawuro | 130 | 0 | 0 | 98 | 75 | 49 | 38 |
| Derashi | 47 | 4 | 9 | 37 | 79 | 6 | 13 |
| Gamo Gofa | 586 | 6 | 1 | 438 | 75 | 142 | 24 |
| Gedeo | 940 | 3 | 0 | 774 | 82 | 163 | 17 |
| Gurage | 461 | 4 | 1 | 224 | 49 | 116 | 25 |
| Hadiya | 1022 | 27 | 3 | 738 | 72 | 258 | 25 |
| Kaffa | 228 | 25 | 11 | 120 | 53 | 83 | 36 |
| Kenbata Tenbaro | 708 | 11 | 2 | 679 | 96 | 18 | 3 |
| Konso | 31 | 3 | 10 | 18 | 58 | 10 | 32 |
| Konta | 23 | 0 | 0 | 12 | 52 | 11 | 48 |
| Sheka | 134 | 1 | 1 | 132 | 99 | 1 | 1 |
| Sidama | 1911 | 25 | 1 | 1421 | 74 | 408 | 21 |
| Silte | 291 | 13 | 4 | 218 | 75 | 44 | 15 |
| South Omo | 123 | 4 | 3 | 103 | 84 | 16 | 13 |
| Wolita | 960 | 19 | 2 | 923 | 96 | 18 | 2 |
| Yeme | 15 | 2 | 13 | 8 | 53 | 4 | 27 |
| Regional | 8502 | 127 | 1 | 6654 | 78 | 1492 | 18 |

## ስጋደዌ መከላከልና ቁጥጥር

የጣምራ ህክምና ከተጀመረ ወዲህ በክልሉ ያለዉ የስጋ ደዌ ገጽታ መሻሻል እየታየበት ቢሆንም ባለፉት አስር አመታት ለህክምና የተመዘገቡ አዲስ ህሙማን ቁጥር አሁንም ቢሆን ከ400 እስከ 600 ድረስ መታይት አሁንም ድረስ ያልተደረሰባቸዉ ዉስን አካባቢዎች እንዳሉ አመላካች ነዉ:: ምንም እንኳን አገልግሎቱ በሁሉም ዞኖች እየተሰጠ ቢሆንም በሽታዉን ለማጥፋት የሚደረገዉን ሂደት ለማፋጠን ይቻል ዘንድ ህብረተሰብ ተኮር የስጋ ደዌ መከላከያ ትግባራት አጠናከሮ በማካሄደ የአዲስ ህሙማን ልየታንማፋጠንን ይጠይቃል:: አዲስ የተመዘገቡ ህሙማን 353 ሲሆኑ በአሁኑ ወቅት በክልሉ ያለዉ የስጋደዌ Disability grade II 14 % ላይ ይገኛል:: የስጋ ደዌ ሕክምና ወስደዉ የዳኑ ደግሞ ከ441 ሕሙማን 348 (80%) ናቸዉ::

የስጋ ደዌ ህሙማን ህክምናቸዉን ከጨረሱ በኋላ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ የሚያስፈልጋቸዉ በመሆኑ ይህን ተግባር በተጠናከረ መልኩ ማስኬድ ይቻል ዘንድ በክልሉ ከፍተኛ የስጋ ደዌ ህሙማን በሚገኙባቸዉ ሁለት ዞኖች የሙከራ ፕሮግራም ተጀምሮ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል:: በዚሁም መሰረት በአሁኑ ወቅት 702 አባላተ ያላቸዉ 42 የአካል ጉዳት መከላከያ ቡድኖች ተቋቁመዉ እንቅስቃሴ እያደረጉ ይገኛሉ:: ይህንንም እንቅስቃሴ ከሚመለከታቸዉ አጋር ደርጅቶች ጋር በመሆን የማሰፋፋት እቅድ በቀጣይ አመት ተይዟል::

### አይነስዉርነት መከላከልና ቁጥጥር

በክልሉ በአሁኑ ወቅት ወደ 155000 የሚጠጉ ከ3ሜትር ባነሰ ርቀት ላይ ሆነዉ ጣቶችን መቁጠር የማይችሉ ወይም ማየት የተሳናቸዉ ሰዎች እንዳሉ ይገመታል(prevalence of blindness being 1.25%) ከ70% በላይ ለሚሆነዉ አይነ ስዉርነት መንስኤዎች ተብለዉ ከሚጠቀሱት የአይን ሞራ ግርዶሽና ካታራክት ቀዳሚዎቹ ናቸዉ:: በህጻንነት የእድሜ ዘመን የሚከሰት አይነስዉርነት ከፍተኛ ቁጥር የሚይዝ ሲሆን ለዚህን በዋነኝነት ኩፍኝ፣ የቫይታሚን ኤ እጥርት በምክንያትነት ከሚጠቀሱት ናቸዉ::

በክልሉ ያለዉን የአይነስዉርነት ጫና ለመቀነስ ይቻል ዘንድ በክልሉ የተለያዩ ዞኖች ዉስጥ በርካታ የመከላከልና የህክምናና የአቅም ግንባታ ተግባራት በአጋር ድርጅቶች እየተከናወኑ ይገኛሉ:: ይህም በመሆኑ በየአመቱ የሚካሄዱ Cataract surgical rate and trichiasis operation ቁጥር ከአመት ወደ አመት እየጠመረ በመሄድ ላይ ይገኛል:: በበጀት አመቱም ለ5092 ህሙማን የካታራክት ቀዶ ጥገና ለ26814 የትረክያሲስ ቀዶ ጥገና ህክምና የተደረገ ሲሆን ለ911972 ሰዎች የዚትሮማክስ ለ116751 ህፃናት የቴትራሳይክሊን አደላ በዘመቻ ከኦርቢስ ኢንተርናሽናል ጋር በመተባበረ የተሰራ ሲሆን ሌሎች ጋረር ድርጅቶች ክርቶፈር ብላይድን ሚሽን፣ ግራርቤት ለድኩማን፣ ፣ አለመአቀፍ የትራኮማ ድርጅትና ላይንስ ክለብ በክልሉ ግንባርቀደም ሆነዉ በመንቀሳቀሰ ላይ ከሚገኙት ከፊሎቹ ናቸዉ::

## የወባ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር

### በኬሚካል የተነከረ አጎበር ስርጭት

የወባ በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረገው እንቅስቃሴ በበጀት ዓመቱ በኬሚካል የተነከረ አጎበር ወባማ አካባቢዎች በሠፈራ መንደሮች በስፋት በማሠራጨትና አጠቃቀምን ለመከታተል የታቀደ ሲሆን በበጀት አመቱም 764,234 የአልጋ አጎበር ተሠራጭቷል:: ሁለት አጎበር ለአንድ አባወራ ስሌት 382,117 የአባወራ የአጎበር ተጠቃሚ ተደርጓል:: ሽፋናችንም በ1998 መጠረሻ ወደ 29% ከፍ ብሏል:: ለአመቱ የተያዘዉም እቅድ ሙሉ በሙሉ ተከናዉኗል::

በክልሉ የሚካሄደውን በኬሚካል የተነከረ አጎበር ስርጭት ውጤታማ ለማድረግ የነፃ አጎበር ስርጭት የአፈፃፀም መመሪያ የተዘጋጀ ሲሆን ይህንን መመሪያ የሚመለከታቸው የዞን ጤና መመሪያ ፣ የወረዳ ጤና ጽ/ቤት እንዲሁም የጤና ተቋማት ባለሙያዎች ተሳታፊ የሆኑባት ስብሰባ በማዘጋጀት የተገመገመ ሲሆን በሚቀጥለው የ1999 በጀት ዓመት ተጠናቆ ስራ ላይ ይውላል :: በተጨማሪም ከግሎባል ፈንድ እንዲሁም ከዩኒሴፍ የተገኘውን ከፍተኛ የሆነ አጎበር ለህብረተሰቡ ወጥና በጤና ላይ ለውጥ ሊያመጣ በሚችል መልኩ እንዲሰራጭ ለጤና ባለሙያዎች ስልጠና በመስጠት ስርጭቱ የተከናወነ ሲሆን የክልሉ ጤና ቢሮም ስርጭቱን ለማገዝ ከህዳር 28 ጠ ታህሳስ 5 ዘመቻ ቀን እንዲሆን በመወሰን ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች በተመረጡ ቀበሌዎች የአጎበር ስርጭት አከናውነዋል ::

ሰንጠረዥ 14: 1998 ጨምሮጠቅላ ላባለፉትአመታት የተሰራጨ አጎበር ብዛትና የአጎበር ሽፋን /2አጎበር ለአንድ አባወራ/ በዞንና ልዩ ወረዳ

| ITNs distribution by Zone & Special Woreda ,1998 EFY,SNNPS | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| SN | Zone/Special woreda | Total Risk Pop. | ITNs distributed in 1998 EFY | Total ITNs Ditributed | ITN Coverage (2ITNs/HH) |
| 1 | Sidama | 1522861 | 119,493 | 163,393 | 26% |
| 2 | Gedeo | 381969 | 25,392 | 39,892 | 26% |
| 3 | Guragie | 479878 | 54,978 | 76,478 | 39% |
| 4 | Hadiya | 681873 | 80,983 | 102,783 | 37% |
| 5 | Silti | 446801 | 51,096 | 66,696 | 37% |
| 6 | Kambata Tambaro | 460593 | 43,153 | 56,753 | 30% |
| 7 | Wolayita | 1468586 | 98,054 | 126,704 | 21% |
| 8 | Gamo Gofa | 1208397 | 67,514 | 100,864 | 20% |
| 9 | Debub Omo | 377042 | 27,080 | 39,980 | 26% |
| 10 | Dawuro | 313542 | 17,400 | 28,100 | 22% |
| 11 | Kaffa | 181378 | 12,400 | 22,700 | 31% |
| 12 | Shaka | 154085 | 15,600 | 23,800 | 38% |
| 13 | Bench maji | 349597 | 57,800 | 72,200 | 51% |
| 14 | Amaro | 112811 | 4,200 | 9,600 | 21% |
| 15 | Burji | 41066 | 1,400 | 3,700 | 22% |
| 16 | Konso | 292432 | 10,900 | 17,750 | 15% |
| 17 | Derashe | 24539 | 4,800 | 7,100 | 72% |
| 18 | Basketo | 15678 | 800 | 6,600 | 105% |
| 19 | Konta | 60514 | 2,200 | 7,500 | 30% |
| 20 | Alaba | 274018 | 45,561 | 63,561 | 58% |
| 21 | Total | 8847660 | 740,804 | 1,036,054 | 29% |

**የወባ ወረርሽኝ መከላከልና ቁጥጥር**

በ1998 በጀት ዓመት በክልሉ በ30 ወረዳዎች በ209 ቀበሌያት የወባ ወረርሽ„ ተከስቶ ወረርሽኙን ለመቆጣጠር ለ 148620 ሰዎች ህክምና ተሠጥቷል:: የተከሠተውን የወባ ወረርሽ„ ለመቆጣጠር ለዞኖችና ልዩ ወረዳዎች የፀረ ወባ ትንኝ ኬሚካል ፣ በኬሚካል የተነከረ አጎበር ፣ የኳርተምና ሌሎች የፀረ ወባ መድሀኒቶች እንዲሁም የቴክኒክ ድጋፍ ተደርጓል ::

| ተ.ቁ | ተግባር | መለኪያ | ዕቅድ | ክንውን | ክንውን በ% |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወረርሽኝ የተከሰተባቸው ወረዳዎች | ቁጥር | 14 | 30 | 214 |
| 2 | ወረርሽኝ የተከሰተባቸው ቀበሌዎች | ቁጥር | 239 | 209 | 87 |
| 3 | ለ ወረርሽኝ የተጋለጠ ህዝብ | ቁጥር | 1192500 | 189637 | 15 |
| 4 | ለወረርሽኝየታከመ ህዝብ | ቁጥር | | 148620 | |

## የፀረ ወባ ትን„ ኬሚካል ርጭት

በ1998 በጀት ዓመት በክልሉ የፀረ ወባ ትንኝ ኬሚካል ርጭት በ443 ቀበሌዎች የተከናወነ ሲሆን 302261 ቤቶች ለመሸፈን ተችሏል ፡፡ የፀረ ወባ ትን„ ኬሚካል ርጭት ለማካሄድ 131795.7 ኪ.ግ 75 ኽ ዲዲቲ 125 ኪ.ግ 100 ኽ ዲዲቲ እንዲሁም 119 ኪ.ግ ማላታይን ጥቅም ላይ ውሏል ፡፡ ከመደበኛ የፀረ ወባ ትንኝ ኬሚካል ርጭት በተጨማሪ ወረርሽ„ን ለመቆጣጠር ርጭት ተከናውኗል ፡፡

| ተ.ቀ. | ተግባር | መለኪያ | ዕቅድ | የ1998 ክንውን | ክንውን በ% |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የተረጨ ቀበሌ | ቁጥር | 400 | 443 | 110.8 |
| 2 | የተረጨ ቤት | ቁጥር | 400000 | 302261 | 75.6 |
| 3 | የተጠበቀ ህዝብ | ቁጥር | 2000000 | 532175 | 26.6 |
| 4 | ጥቅም ላይ የዋለ 75 % ዲዲቲ | ኪ.ግ | 138666 | 131795.7 | 95.0 |
| 5 | ጥቅም ላይ የዋለ 100 ኽ ዲዲቲ | ኪ.ግ | 1000 | 125 | |
| 6 | ጥቅም ላይ የዋለ ማላታይን | ኪ.ግ | 13866 | 119 | 11.9 |

## ምርመራና ህክምና

በ1998 በጀት ዓመት 500,000 ሰዎች ለማከም ታቅዶ 769,015 ሰዎች ህክምና የተሠጠ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 523,572 /75%/ ሰዎች በወባ ህመም ስሜት 177,484 /25 %/ ሰዎች በደም ምርመራ ህክምና ያገኙ ናቸው ፡፡ በደም ምርመራ ህክምና ካገኙት ውስጥ ፕላስሞዲየም ፋሊሲፓረም 121,045 /68% / ፣ ፕላስሞዲየም ቫይቫክስ 52,552 / 29% /፣ ፕላስሞዲየም ማሌሬ 702 / 0.39% / ድብልቅ 4,212 / 2% / ያህል ናቸው ፡፡

| ተ.ቁ | ተግባር | መለኪያ | ዕቅድ | የ1998 ክንውን | ክንውን በ% |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በህመም ስሜት የታከሙ | ቁጥር | 250,000 | 545,407 | 218 |
| 2 | የተመረመረ የደም ናሙና | ቁጥር | 325,000 | 363,463 | 112 |
| 3 | በምርመራ ወባ የተገኘባቸው | ቁጥር | 250,000 | 181,976 | 73 |
| 4 | ፕፋ | ቁጥር | 150,,000 | 123739 | 82 |
| 5 | ፕቫ | ቁጥር | 75,000 | 53,309 | 71 |
| 6 | ፕማ | ቁጥር | 1,250 | 716 | 57 |
| 7 | ድብልቅ | ቁጥር | 1,250 | 4,212 | 337 |
| 8 | ጠቅላላ የታከሙ | ቁጥር | 500,000 | 727,383 | 145 |

## የአካባቢ ጤና አገልግሎት

በአካባቢ ጤና አገልግሎት ዘርፍ ትኩረት ተሰጥቶ ከተከናወኑት ተግባራት ቀዳሚዎቹ በ1997 በጀት ዓመት የተደረሰበትን 86% የመፀዳጃ ቤት ሽፋን ወደ 90% ማድረስ ፣ የመፀዳጃ ቤት አጠቃቀምን ባህል በማሳደጉና የተሠሩ መፀዳጃ ቤቶችን ጥራትን በማሻሻሉ ዙሪያ ተከታታይነት ያለው ተግባራዊ እንቅስቀሴ ማከናወን ዋና ዋናዎቹ ናቸው ፡፡ በበጀት አመቱ የተያዘዉ እቅድ ስኬታማ ማድረግ ተችሏል፡፡ ይሁንና የመፀዳጃ ቤቶችን ጥራት ማሳደግ ፣ የአጠቃቀም ፋይዳው ላይ አሁንም የበለጠ የጋራ መግባባት መፍጠርና ከመፀዳጃ ቤት ውጪ መፀዳዳት እንደባህል የሚወገዝበትን ማህበረሰብ የመፍጠር ጉዳይ አሁንም ትኩረትና የሁላችንንም ርብርብ የሚፈልግ ነው ፡፡

## የተቀናጀ የበሽታዎች ቅኝት

በአገር አቀፍ ደረጃ ልዩ ክትትል የሚደረግባቸዉ 22 ዋና ዋና በሽታዎች **ቅኝት** በተጠናከረ መልኩ በክልሉ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ይሁንና በአገር አቀፍና በክልል ደረጃ ቅድሚያ ተሰቷቸዉ የቅርብ ክትትል ከሚደረግባቸዉ በቀዳሚነት ( AFP and Measles surveillance) ፈጣን የጡንቻ መዛል የኩፍኝ በሽታ አሰሳና ክትትል ተጠናክሮ እየተካሄደ ነወ፡፡

### የፖሊዮ በሽታ ቅኝት

በበጀት አመቱ ክልሉ ሪፖርት ማደረግ የሚጠበቅበት ቁጥር = 143

በበጀት አመቱ ሪፖርት የተደረጉ ብዛት = 148

Non-polio AFP Rate= 2.05

### የኩፍኝ በሽታ ቅኝት

በበጀት አመቱ ክልሉ ሪፖርት ማደረግ የሚጠበቅበት ቁጥር = 149

በበጀት አመቱ ሪፖርት የተደረጉ ብዛት = 357

Measles case detection rate= 2.4

### የቅኝት ሪፖርት

| | የተቀመጠ ግብ | ክንዉን |
|---|---|---|
| ወቅታዊነት /(Timeliness) | 90% | 91% |
| የሙሉነት (completeness) | 90% | 94% |

### የወረርሺኝ ቁጥጥር

በ1998 በጀት አመት በክልላችን የማጅራተ ገትር ወረርሺኝ በ6 ዞኖችና በኮንሶ ልዩ ወረዳ በድምሩ 15 ወረዳዎች የተጠቁ ተጠቅተዋል፡፡ በድምሩ በወረርሺኙ 664 ሰዎች ተጠቅተዋል፣ 22 በወረርሺኙ ምክንያት ሞተዋል፡፡ ወረርሺኙንም ለመግታት በተደረገዉ ጥረት ከ 570,082 በላይ ሰዎች የመከላከያ ክትባት እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡

ሰንጠረዥ15:ZoneandspworedaIDSRCoverage(TimelinessandCompleteness) SNNPRs,1998 EFY

| | Zone and sp.woreda IDSR Coverage ( Timeliness and Completeness) SNNPRs,1998 EFY | | |
|---|---|---|---|
| | Zone/sp.woreda | % Timiliness | % completeness |
| 1 | Bech Maji | 49% | 64% |
| 2 | Dawro | 54% | 63% |
| 3 | Gamogofa | 95% | 95% |
| 4 | Gedeo | 97% | 98% |
| 5 | Gurage | 96% | 97% |
| 6 | Hadiya | 92% | 93% |
| 7 | Kaffa | 81% | 86% |
| 8 | Kembata Tembaro | 97% | 98% |
| 9 | Sheka | 94% | 96% |
| 10 | Sidama | 91% | 91% |
| 11 | Silte | 91% | 97% |
| 12 | Debub Omo | 97% | 100% |
| 13 | Wolayita | 100% | 100% |
| 14 | Alaba | 100% | 100% |
| 15 | Amaro | 100% | 100% |
| 16 | Basketo | 97% | 100% |
| 17 | Burji | 100% | 100% |
| 18 | Dirashe | 100% | 100% |
| 19 | Konso | 100% | 100% |
| 20 | Konta | 91% | 91% |
| 21 | Yem | 100% | 100% |
| 22 | Awassa city Adm | 83% | 100% |
| | Region | 91% | 94% |

## የመደበኛ ጤና አገልግሎት አቅርቦት

### የፈውስ ሕክምና

በዚህ የአገልግሎት ዘርፍ በ1998 በመንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት የተከናወኑ የተመላላሽ፣ተኝቶ ሕክምና፣ የቀዶ ህክምናና የተለያዩ የላቦራቶሪና ሌሎችም የምርመራ አገልግሎቶች አፈጻጸም ይቀርባል:: በበጀት አመቱ በጤና ጣቢያ ፣ ታዳጊ ጤና ጣቢያ፣ የመያድ ክሊኒኮችና ሆስፒታሎች የተመላላሽ አገልግሎትን /አዲስና ድጋሚ/ ለ3,609,280 ተገልጋዮች

ለመስጠት ታቅዶ አገልግሎቱን ለ3,299,294 (80%) ተጠቃሚዎች ለመስጠት ተችሏል::

አገልግሎቱን ካገኙትም 2,412,517 አዲስ ሕሙማን ሲሆኑ 886,777 በድጋሚ አገልግሎቱን ሊጠቀሙ የቻሉ ናቸው:: በበጀት ዓመቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ጤና ተቋማት በመምጣት የተመላላሽ ሕክምና ካገኙት ውስጥ ወደ ጤና ጣቢያ በመምጣት አገልግሎቱን ማግኘት የቻሉት 1,900,393 ናቸዉ:: የጤና ጣቢያ ተጠቃሚ ሽፋን ስንመለከት በ1995 5% ፣ በ1996 6% ፣ በ1997 መጨረሻ ወደ 7.2% ና በ1998 መጨረሻ ወደ 12% ለማደግ ችሏል:: አጠቃላይ የተመላላሽ አገልግሎትን ያለፉትን አመታት ስንመለከት በ1993 2,152,261፣ በ1994 2,095,009፣ በ1995 2,144,844 በ1996 2,886,624 ሲሆን ይህ አሀዝ በ1997 ወደ 3,037,369 እና በ1998 ወደ 3,299,294 ከፍ ሊል ችሏል::

የተመላላሽ አገልግሎት ተጠቃሚነትን ያለፉትን አመታት አፈጻጸሞች ስንመለከት በ1995 0.11new visit/person/year እና 0.15 allvisit/per/person/yr. የነበረዉ በ1996 መጨረሻ 0.14new visit/person/year እና 0.20 allvisit/per/person/yr የደረሰ ሲሆን በ1997 allvisit/per/person/yr ከ1996 ጋር ሲነጻጸር ለዉጥ አልታየበትም::በ1998 በጀት አመት ግን የተሻለ አፈጻጸም ለማየት ተችሏል 0.16New visit/person/year እና 0.22 allvisit/per/person/yr ::



በበጀት አመቱ የተኝቶ ህክምና፣ የላቦሯቶሪና የቀዶ ህክምና አገልግሎትን ለ68,121፣ 643,953፣ 21,220 እንደቅደም ተከተላቸዉ ለመስጠት ታቅዶ የተኝቶ ህክምና ለ87,163፣ የላቦራቶሪ አገልግሎትን ለ801,853 እና የቀዶ ህክምና አገልግሎትን ለ25,886 ተገልጋዮች ለመስጠት ተችሏል:: በበጀት አመቱ ወባ፣ሳንባ ምችና የሳንባ ነቀርሳ በተመላላሽም ሆነ በተኝቶ ህክምና ቀዳሚዉን ደረጃ የያዙ በሽታዎች ናቸዉ:

## የጤና አገልግሎት ማደራጃ

በዚህ የገልግሎት ዘርፍ ትኩረት ተሰቷቸዉ የሚከናወኑ ተግባራት በተመለከተ የመንግስት ጠ ና ድርጅቶችን ከማደራጀት አንሰቶ ቀልጣፋና ዉጤታማ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል አሰራሮችን ለማስረጽ የሚያስችሉ ስልቶችን ማፈላለግና ማስተዋወቅ አካቶ የግልና ግብረ ሰናይ ጠ ና ድርጅቶች መደገፍና መቆጣጠር ያካተታል:: በበጀት አመቱምበዚህ አገልግሎት ዘርፍ ቡድኑን ከማደራጀተ አንስቶ ለማከናወን ትኩረት የሰተጣቸዉ ጉዳዮች የመንግስት ጤና ድርጅቶችን የህክምና መሳሪያ አቅርቦትና ያሉበትን ደረጃ የመቃኘት፣ በመንግስት፣ በግልና መንግስታዊ ባልሆኑ ጤና ድርጅቶች ድጋፋዊ ክትትል የማደረግ፣በየጤና ድርጅቶች ዉስጥ የሲ/ስ/ማሻሻያ ፕሮግራም ስርጸትና ትግበራ ዳሰሳ ማካሄድ፣ የበሽተኞችን የቅብብሎሽ ስርአት ትግበራ ምን ገጽታ እንዳለዉና ለዚሁ አጋዝ ሰነድ የማዘጋጀትና የማሰተቸት ተግባራት ቀዳሚ ትኩረት የተሰጣቸዉ ነበሩ::

በበጀትአመቱም በቢሮ ደረጃ ይህ ዘርፍ ባለዉ የባለሙያ እጥረት የተነሳ ዘርፉ በባለሙያ ያልተደራጀ መሆኑን ከግንዛቤ በመዉሰድ ዘርፉን የማደረጀትና ስራ ቅድሚያ ትኩረት ተሰቶች ለማደራጀት ጥረቶች ተካሂደዋል:: ከዚህ በተጓዳኝ በእቅድ ከተያዙት የመንግስት ሆስፒታሎት የህክምና መሳሪያዎች ችግር በሚመለከት የቆጠራና ምዝገባ፣ የግል ጤና  ድርጅቶች ድጋፋዊ ክትትል፣ የመንግስት ጤና ድርጅቶች መዋቅር ቅኝት፣ የበሽተኞች ቅብብሎሽ አተገባበር መመሪያና የበሽተኞች ማስተላለፊያ ቅጽ ዝግጅትና የመንግስት ሆስፒታሎችና የተመረጡ በግል ክሊኒኮች ዙሪያ በተደረገዉ ድጋፋዊ ክትትል በክልላችን ፋይዳ ያለዉ የግል ተቋሞች እንዳሉ ያሳያል ቢሆንም ተመጣጣኝ ክትትልና ድጋፍ አንጻር ገና ብዙ መሰራት እንዳለበት አመላክቷል:: አሁን ባለን መረጃ 273 የተለያየ ደረጃ ያላቸዉ የግል ተቋማት እንዳሉ ያሳያል /ሰንጠረዠ /እነዚህን አብዝቶ መጠቀም መቻል የሕዝባችንን ጤና ከመጠበቅ አልፎ የዘርፉን አላማ ለማሳካትሚና እንደሚጫወት ይታመናል::

### የጤናዉ ሴክተር ገቢ ማሻሻል

የጤናዉን ሴክተር የገቢ አቅም በማጠናከር የሚሰጠዉን አገልግሎት ጥራት ማሻሻል ይቻል በክልሉ ምክር ቤት ለፀደቀው የጤና አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር አዋጅ ደንብ ተጠናቆ

ወቷል፡፡በበጀት አመቱም ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያዎች ተዘጋጅተዉ ለአስተያየት ተሰራጭተዋል፡፡ በበጀት አመቱን አዋጁንና ደንቡን እንዲሁም ዝርዝር መመሪያዎችን በቀጣይ በተዋረድ ላሉ ባለሙያዎች ማስተዋወቅና ቀጣይ ስልጠናዎችን የሚሰጡ አሰልጣኖች ሰልጥነዋል፡፡ ከስልጠናዉም በመቀጠል ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች በአዋጁና በደንቡ ዙሪያ ለባለሙያዉና ለፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ባለሙያዎች የማስተዋወቅ ተካሂዷል፡፡ በቀጣዩም አመት የሚካሄድ ይሆናል፡፡

### የአገልግሎት ማሻሻያ ትግበራ

የጤናዉን ሴክተር አገልግሎት አቅርቦት ተገልጋይ ተኮር በሆነና በተሻለ መልኩ ማገልገል ይቻል ዘንደ ቀደም ሲል በተጠናቀቀዉ የአገልግሎት ማሻሻያ ጥናት ላይ የተቀመጡትን የማሻሻያ አስተያየቶች መሰረት በማደረግ የማስተካከያና የማሻሻያ ተግባራት ተከናዉነዋል፡፡
በማሻሻያዉ ጥናት መሰረትም የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ተካናዉነዋል፡
-የመዋቅር ማሻሻያ፣
-የጋራዥ ግንባታ፣
-ክፍት የስራ መደቦችን በሰዉ ኃይል እንዲሟሉ የማደረግ፣
-ማህደርና ሪኮርድ አሰራርን የማሻሻል የመጀመሪያዉ ደረጃ፣
-ክፍሎችን በአስፈላጊ መሳሪያዎች የማደራጀት/ኮምፒዉተር/
-የባለሙያ አቅም ግንባታ ስልጠና /የተለያዩ የዲፕሎማና የዲግሪ ፕሮግራሞች/
-ድጋፊዊ ክትትል
-ወርሃዊ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ
-የሲ/ሰ/ማ/ፕሮግራም ትግበራ ቅኝት ከፌዴራል አቅም ግንባታ ሚ/ጋር በመሆን ተካሂዷል፡፡

## ጤና ተቋማትን ማስፋፋትና ማጠናከር

### በሕብረተሰብ ተሳተፎ የጤና ኬላዎች ግንባታ

የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራማችንን ተቋማዊ ለማድረግ መሠረታዊ ጤና አገልግሎት ተቋማት ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህንንም እቅድ በህብረተሰብ ተሳትፎ እዉን ማድረግ ይቻል ዘንድ በ1997 እና በ1998 በጀት ዓመት ከ2272 በላይ ጤና ኬላዎች ግንባታ በመካሄድ ላይ ሲሆን በበጀት አመቱ በተደረገዉ ከፍተኛ ርብርብ 1372 ጤና ኬላዎች ተጠናቀዉ ለአገልግሎት ዝግጁ ሆነዋል፡፡ በበጀት አመቱ መጨረሻም በአጠቃላይ በክልሉ 1828 ጤና ኬላዎች ይኖራሉ ተብሎ ይገመታል፡፡

የጤና ኬላና የታዳጊ ጤና ጣቢያዎችን ግንባታ ሂደት አፈጻጸም ክትትል በተመለከተ የክልሉ የጤና መማክርት ም/ቤት በየወሩ በሚገናኝበት ወቅት ቀዳሚዉ የክትትል አጀንዳ በማድረግ የቅርብ ክትትል በመደረጉ በበጀት አመቱ የተሻለ አፈጻጸም ለማስመዝገብ ተችሏል፡፡ ይሁንና የጤና ኬላዎቹ ግንባታ በተጠበቀዉ የጊዜ ሰሌዳ ለማጠናቀቅ የሲሚንቶ እጥረት የበኩሉን አሉታዊ አስተዋጽዎ አበርክቷል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በ1997 በጀት አመት ሲሰጥ የነበረዉ

ትኩረት፣ድጋፍና ክትትል በዞንና በወረዳ ደረጃ በመቀነሱ በተለይም የታዳጊ ጤና ጣቢያዎች ክንዉን ተጓክሟል::

## ነባር የአይዲኤና ኤዲኤፍ ፕሮጀክቶች

በበጀት ዓመቱም ግንባታቸው ሲካሄድ የነበሩ ነባር ፕሮጀክቶችን የማጠናቀቅ ተግባራት ትኩረተ ተሰጥቷቸው የተከናወኑ ሲሆን 2 ጤና ጣቢያ፣4ጤና ኬላዎች፣ 8 የተማሪዎች የመስክ ማቆያዎችና ርክክብ ተደርጓል::

ከኤዲአፍ በተገኘ ብድርና በመንግሥት ማቺንግ ፈንድ በጀት ግንባታቸው በመካሄድ ላይ ላሉ ፕሮጀክቶች የፈርኒቸር ግዥን ጨምሮ በበጀት አመቱ ከመንግስትና ከአበዳሪዉ ድርጅት በድምሩ 5,568,784( ለግንባታ 3,546,347 ለፈርኒቸር 2,022,437 ) ብር ክፍያ ተፈጽሟል:: ከዚህ ውስጥ 4,190,508 ብር ከኤዲኤፍ ከብድር ሲሆን ቀሪው 1,378,276 ከመንግሥት ግምጃ ቤት ነው :: ከዚህ በተጨማሪ ለተማሪዎች የመስክ ማቆያ የተመደበዉ 86 662 በስራ ላይ ዉሏል፣ የአማን የነርስ ማ/ት/ቤት ከመንግሥት ግምጃ ቤት የተመደበዉ 1868750 ብር በስላ ላይ ዉሏል/ 561285 በዝዉዉር ለታክስ ክፍያ፣ 330515 ለቀጣይ ፌዝ ግንባታ አድቫንስ ክፍያ፣271835 ለነባር ግንባታ ክፍያ፣357544 ተዟዉሮ ለኤዲቢ ፕሮጀክት ማቺንግ ፈንድና 47849 ብር ደግሞ ለተቋሙ መብራት ማስገቢያ በስራ ላይ ዉሏል/::

## የጤና ተቋማት ስርጭት

በ1998 የበጀት ዘመን በክልሉ ከአንድ ሺህ ሶስት መቶ ሀያ በላይ አልጋ ያላቸዉ 19 ሆስፒታሎች ፣/ 12 የመንግስት፣4 የመያድ፣ 1 የግልና 1 በትምህርት ሚኒስቴር የሚተዳደር ሪፈራል ሆስፒታል/፣ 161 ጤና ጣቢያዎች / 157 የመንግሥት፣ 4 መንግስታዊ ያልሆኑ / ፣ 194 ታዳጊ ጤና ጣቢያዎች እና 1876 ጤና ኬላዎች ይገኛሉ :: የጤና ሽፋኑም በ1998 መጨረሻ ወደ 73.5%% አድጓል::



| Type of HF | required as per the standard | available | Gap | HF:popn.ratio |
|---|---|---|---|---|
| HC | 596 | 161 | 435 | 1:92,559 |
| HP | 2980 | 1876 | 1104 | 1:7944 |
| DH | 60 | 10 | 50 | 1:1.49mill. |
| ZH | 15 | 6 | 9 | 1:2.5mill. |

ከነዚህ በተጓዳኝ ለህብረተሰቡ ከፍተኛ አገልግሎት በመስጠት የክልሉን የጤና አገለግሎት አቅርቦት በማሻሻሉ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ያሉ በግል ባለሀብቶች የሚንቀሳቀሱ 20 ፋርማሲዎች፣ 69 መድሃኒት መደብሮች፣421 ገጠር መድሃኒት ቤቶች፣-እንዲሁም 217 (2ልዩ፣10 ከፍተኛ፣30 መካከለኛ፣175 አነስተኛ ደረጃ ያላቸው ) የግል ክሊኒኮች፣ 25 የግል ዲያግኖስቲክ ላቦራቶሪዎች፣ 47 የኤንጂኦ ና 34 ተተቋም ክሊኒኮች አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

በክልሉ በአሁኑ ወቅት አንድ ጤና ጣቢያ በአማካይ ለ 92,559 ሰዎች/ስታንዳርድ 25,000/፣ አንድ ጤና ኬላ ለ 8,152 ሰዎች/ስታንዳርድ 5,000/ ፣አንድ የዲስትሪክት ሆስፒታል ለ 1.49 ሚሊዮን ሰዎች/ስታንዳርድ 250,000/ና አንድ የዞን ሆስፒታል ለ2.5 ሚሊዮን ሰዎች/ስታንዳርድ 1,000,000/ ፣አገልግሎት ይሰጣሉ ተብሎ ይገመታል፡፡

# የሰው ኃይል ልማት

## መደበኛ ስልጠና

በክልላችን ያለውን የባለሙያ ፍላጐት ለማሟላት በሚደረገው ጥረት በበጀት ዓመቱ 1050 አዲስ ሰልጣኞችን ለመቀበል ታቅዶ 1164(110%) አዲስ ሠልጣኞች በ10+3 ፕሮግራም ከዞኖችና ልዩ ወረዳዎች ተመልምለው ወደየተቋማቱ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ከነዚህ ሠልጣኞች ውስጥ 61% ሴቶች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል 401 ተማሪዎች ከሰርተፊኬት ወደ ዲፕሎማ የሙያ ማሻሻያ በየሆስፒታሎች እንዲማሩ ለማድረግ ታቅዶ 552 (137%) ተከናዉኗል ፡፡

ሰንጠረዥ 16 : በ1998 **በጀት አመት ወደ ጤና ሳይንስ ኮሌጆች የገቡ ሰልጣኖች ብዛትና ጾታዊ ስብጥር**

| ተቁ | የሰልጣኞች ሙያ(10+3) 1998 የገቡ | ኮሌጆች | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዋሳ | | | አ/ምንጭ | | | ሆሳዕና | | | ጠቅላላ | | |
| | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| 1 | ክሊኒካል ነርስ | 60 | 123 | 183 | 53 | 52 | 105 | 80 | 81 | 161 | 193 | 256 | 449 |
| 2 | ፐብሊክ ነርስ | 30 | 29 | 59 | 75 | 74 | 149 | 33 | 29 | 62 | 138 | 132 | 270 |
| 3 | አዋላጅ ነርስ | 0 | 113 | 113 | 0 | 50 | 50 | 0 | 106 | 106 | 0 | 269 | 269 |
| 4 | ፋርማሲ ቴክኒሻን | 40 | 22 | 62 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 40 | 22 | 62 |
| 5 | ላቦራቶሪ ቴክ | 31 | 31 | 62 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 31 | 31 | 62 |
| 6 | አካባቢ ጤ/አገ | 29 | 23 | 52 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 29 | 23 | 52 |
| | ድምር | 190 | 228 | 531 | 128 | 126 | 304 | 113 | 110 | 329 | 431 | 733 | 1164 |

የአርባ ምንጭ፣ የሆሳዕናና የአዋሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጆችን የመቀበል አቅም ለማሳደግ ይቻል ዘንድ በበጀት አመቱ በሶስቱም ተቋማት ግቢ ዉስጥ ለመስራት የታቀዱ ተጨማሪ ህንጻዎች ግንባታ በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ ዝርዝር አፈጻጸማቸውን በተመለከተም የአዋሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ግንባታ 70% ፊዚካል ስራ ለማከናዉን ታቀዶ 45% ፣ የሆሳእና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ 70% ፊዚካል ስራ ለማከናውን ታቀዶ 35% ፣ የአርባምንጭ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ግንባታ 70% ፊዚካል ስራ ለማከናወን ታቅዶ 27% ተከናውኗል፡፡

መንግሥት በፈጠረው ምቹ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ መሠረት በመደበኛ ሥልጠና በክልሉ

ባለሀብቶች የተቋቋሙ የግል ጤና ሳይንስ ኮሌጆች ከክልሉ ቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ኮሚሽን ቅድመ ዕውቅና ተሰጥቷቸው በተለያዩ ሙያ ዘርፎች በማስተማር ላይ የሚገኙ ሲሆን በ1997 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ከጀኔራል ፓራሜዲካል ኮሌጅ እና ከሜድኮ ባዮ ሜዲካል ኮሌጅ የተመረቁ ባለሙያዎች ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሙያና ሥራ ፈቃድ ምስክር ወረቀት አቅርበው በክልሉ ባሉ ጤና ድርጅቶች የሥራ ሥምሪት አግኝተዋል፡፡በአሁኑ ወቅትም በክልሉ በጤና ሙያ መስመር በማስተማር የሚገኙ የግል ጤና ሳይንስ ኮሌጆችና የሚያስተምሩት የሙያ ዘርፍ በተሰጣቸው ቅድመ ዕውቅና እና ዕውቅና ከዚህ በታች ተመልክተዋል፡፡

| ተ.ቁ | የኮሌጅ ስም | የሙያ ዘርፍ | ዕውቅና ደረጃ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ጀኔራል ፓራሜዲካል ኮሌጅ | ክሊኒካል ነርስነት | 10+1 10+2 | እዉቅና |
| | | | 10+3 | እዉቅና |
| | | ላቦራቶሪ ቴክኒሻን | 10+1 | ቅድመ እዉቅና |
| | | | 10+3 | እውቅና |
| | | ፋርማሲ ቴክኒሽያን | 10+2፣ 10+3 | እዉቅና |
| 2 | ሜድኮ ባዮሜዲካል ኮሌጅ | ክሊኒካል ነርስነት | 10+1,10+2,10+3 | ዕውቅና |
| 3 | ስሊሆም ነርስ ትምህርት ቤት | ክሊኒካል ነርስነት | 10+1፣ 10+2, እና 10+3 | ዕውቅና |
| | | ፋርማሲ ቴክኒሻን | 10+2, | ቅድመ እዉቅና |
| 4 | ሴንተራል ጤና ኮሌጅ | ክሊኒካል ነርስነት | 10+3 | ቅድመ እዉቅና |
| 5 | አሌፍ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ | ክሊኒካል ነርስነት | 10+3 | ቅድመ እዉቅና |
| | | ላቦራቶሪ ቴክኒሻን | 10+3 | ቅድመ እዉቅና |
| | | ፋርማሲ ቴክኒሽያን | 10+3 | ቅድመ እዉቅና |
| 6 | ፋርማ ጤና ማ/ተቋም | ፋርማሲ ቴክኒሽያን | 10+2 | ዕውቅና |
| 7 | ሳች ዱና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ | ክሊኒካል ነርስነት | 10+1 , 10+2, 10+3 | ቅድመ እዉቅና |
| | | | | |
| | | ፋርማሲ ቴክኒሽያን | 10+2 , 10+3, | ቅድመ እዉቅና |
| 8 | ትሮፒካልጤና ሳይንስ ኮሌጅ | ክሊኒካል ነርስነት | 10+1 , 10+2, 10+3 | እዉቅና |
| | | ፋርማሲ ቴክኒሻን | 10+2, 10+3 | ዕውቅና |
| | | | | |
| 9 | ቤቴል ሶሊዳሪቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ | ክሊኒካል ነርሲንግ | | ቅድመ እዉቅና |
| | | | | |

## ሙያ ማሻሻያ ስልጠና

በክልሉ ያለውን ከፍተኛ የባለሙያ እጥረት ማሟላት ይቻል ዘንድ በዚህ የአገልግሎት ዘርፍ በመደበኛዉ የስልጠና ፕሮግራም በክልሉ ጤና ቢሮ ስር ያሉ የጤና ሳይንስ ኮሌጆች የመቀበል አቅማቸዉን እንዲያሳድጉ በማድረግና በሰዉ ኃይልና በማቴሪያል በማጠናከር ከቀድሞዉ የተሻለ የሰልጣኝ ቁጥር መቀበል እንዲችሉ በማድረግ ያለዉን የባለሙያ እጥረት ለማቃለል በበጀት አመቱ ጥረት ተደርጓል፡፡ የጤና ሳይንስ ኮሌጆችን የመደበኛ ስልጠና ፕሮግራም ላይ ጫና በማይፈጥር መልኩ የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎች የሚካሄዱበትን ስልት መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ በመገመቱ በተለይም ከሰርቲፊኬት ወደ ዲፕሎማ የሚሰጠዉ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና በሆስፒታሎች ዉስጥ እንዲሆን የጋራ መግባባት ላይ ተደርሶ ለዚህም መደረግ ያለበት ቅድመ ሁኔታዎች እንዲስተካከሉ ከተደረገ በኃላ በ1997 የተጀመረዉ ስልጠና በዚህም አመት ተጨማሪ ሰልጣኞችን በመቀበል

ቀጥሏል፡፡

በበጀት አመቱ 80 ጤና ረዳቶችን ወደ ክሊኒካል ነርስነት ለማሰልጠን ታቅዶ 78(62ወንዶችና 16 ሴቶች)ለመቀበል ተችሏል፡፡ቀደም ሲል በሰርቲፊኬት የተመረቁ ባለሙያዎችን ወደ ዲፕሎማ የማሳደግ ስልጠና ፕሮገራም በበጀት አመቱም አየተካሄደ ሲሆን በዚህ ዘርፍ በበጀት አመቱ በጥቅሉ 300 ሰርቲፊኬት ምሩቃን ለመቀበል ታቅዶ በበጀት አመቱ 195 /143 ወንድና 52 ሴ/ ፈተናዉን አልፈዉ ስልጠና ጀምረዋል፡፡ በዚሁ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና ረገድ ከዲፕሎማ ወደ መጀመሪያ ዲግሪ ፕሮግራም 5 ዲፕሎማ ምሩቃን (3BSc ophthalmology & 3 Nurse) ትምህርታቸዉን እየተከታተሉ ይገኛሉ፡፡ ሶስት ባለሙያዎችም በክትትልና ግምገማ ላይ የማስተርስ ስልጠና በጂማ ዩኒቨርሲቲ በመከታተል ናቸዉ፡፡

በበጀት አመቱም በተልዕኮ ርቀት ስልዕጠና ፕሮግራም በጎንደር ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በተጀመረዉ ሞጁላር የኤምፒኤች የማስተርስ ስልጠና ፕሮግራም 12 ባለሙያዎች /8 ነባርና 8 አዲስ/ ትምህርታቸዉን በመከታተል ላይ ናቸዉ፡፡

በአገራችንም ሆነ በክልላችን የእናቶችና ህጻናት ሞት መጠን በጣም ከፍተኛ መሆኑ ይታወቃል ፡፡ ለዚህን ከሚጠቀሱት ምክንያቶች የሚካተተዉ በእርግዝናና ከወሊድ ጋር ተያይዘዉ ለሚመጡ ድንገተኛ የጤና አገልግሎቶችን በቀረቤታ ሆነዉ አገልግሎት የሚሰጡ በቂ ክህሎትና ዝግጁነት ያላቸወ ባለሙያዎች በየጤና ጣቢያዎች ላይ እንዲኖሩ ማደረግ አለማቻላችን ተጠቃሽ ምክንያት ነዉ ፡፡ ይህን ከግንዛቤ በመዉሰድ ያለዉን የባለሙያ እጥረት መቅረፍ ይቻል ዘንድ በክልላችን ባሉ ሆስፒታሎችና ከደቡብ ዩኒቨርሲቲ ጋር በጋራ በመሆን የመጀመሪያ ዙር 300 የጤና መኮንን ስልጠና ፕሮግራም በ1997 መጀመሩ ይታወሳል፡፡ በበጀት ዓመቱ በ1997 የተጀመረዉን የተፋጠነ የጤና መኮንኖች ሥልጠና ሂደት ከሐዋሳ ዩኒቨርሲተና ከፌዴራል ጤና ጥበቃ ጋር በመሆን የቅርብ ክትትል የማድረጉ ስራ በቅንጅት ተከናዉኗል፡፡

በባለሙያ ስምሪት ረገድ በበጀት አመቱ 1500 ሁለተኛ ዙር የጤና ኤክስቴንሺን ባለሙያዎች ወደ ስራ እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡ የመጀመሪያ ዙር 747 የጤና አጠባበቅ ኤክስቴንሽን ሰራተኞችንና በ1998 በጥር ወር ተመረቁትን 1500 ጨምሮ በድምሩ 2246 ሁለት ወር የሙያ ክህሎት የማጠናከሪያ ስልጠና ከተሰጣቸዉ በኃላ ተመርቀዉ ወደ ተግባር እንዲገቡ የተደረገ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች የጤና ኤክስቴንሺን ባለሙያዎች ቁጥር ወደ ስራ ከተሰማሩ በኋላ የመቀነስ አዝማሚያ እያሳየ በመሄድ ላይ መሆኑን በበጀት አመቱ የተገኘዉ ሪፖርት ያመላክታል በዚሁም መሰረት ቁጥራቸዉ ወደ 2199 ዝቅ ብሏል፡፡

በ1997 በጀት አመት ለሙያ ማሻሻያ ከገቡት ባለሙያዎች ዉስጥ በበጀት አመቱ ከሶስቱ የጤና ሳይንስ ኮሌጆች በድምሩ 387/276 ወንድና 111 ሴት/ ባለሙያዎች የሙያ ማሻሻያ ስልጠና ጨርሰዉ ተመርቀዋል፡፡ ከነዚህም 295 ክሊኒካለ ነርስ፣35 ፐብሊክ ሄልዝ ነርስ፣29 ድራጊስትና 28 ሜዲካለ ላቦራቶሪ ቴክኒሻን ናቸዉ፡፡

**የጤና ባለሙያ ስርጭት**

በ1998 በክልሉ በጠቅላላው 3711 ( 2735 ወንድና 976 ሴት ) የጤና ኤክስቴንሺን ባለሙያዎችን ሳይጨምር የጤና ባለሙያዎች አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ሲሆኑ ከነዚህም 110 ሐኪም / ሁሉም ዓይነት / 2945 ነርሶች / ሁሉም ዓይነት / ፣289 ጤና ረዳቶች ፣11 ፋርማሲስቶች ፣ 215 ጤና መኮንኖች ፣ 248 ጤና ተቆጣጣሪዎች /፣ 250 ፋርማሲ ቴክኒሽኖችና ድራጊስቶች፣ 304

ላቦራቶሪ ቴክኒሽኖችን /ጁነየሪና ሲኒየሪ/ ከሚጠቀሱት ሲሆኑ በክልላችን በአሁኑ ወቅት አንድ ነርስ በአማካይ ለ 5060 ፣ አንድ ሀኪም ለ135,472 ሰዎች በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ ጥምርታ አንድ ሀኪም ለ10,000 እና አንድ ነርስ ለ5,000 ሰው ከሚለው የዓለም ጤና ድርጅት መስፈርት በጣም የተራራቀ ነው፡፡ የጤና ባለሙያና የሕዝብ ጥምርታ አለመጣጣም እንደተጠበቀ ሆኖ ፍትሐዊና ግልፅ የሆነ የምደባ ፣ የሥልጠና ፣ የዝውውር እና የስንብት ሥርዓት አለመኖር የባለሙያን የሥራ ተነሳሽነትን ከሚጠበቀው በታች እንድሆን አድርጓል፡፡






## የባለሙያ ቅጥርና ስንብት

በበጀት አመቱ በክልሉ ጤና ቢሮ በኩል የተፈጸመ የባለሙያዎች ቅጥር በጣም አነስተኛ ነዉ:: ይህም የሆነበት ዞኖች ባለሙያዎችን እራሳቸዉ መቅጠር በመጀመራቸዉ ምክንያት ነዉ::በበጀት አመቱም በቢሮ አማካኝነት 7ሀኪሞች፣42 ክሊኒካልነርሶች፣5 ጤና መኮንን፣12 ድራጊስት፣3 ሜዲካል ላቦራቶሪ ቴክኖሎጂስት፣አንድ ጤና ተቆጣጣሪና አንድ ፐብሊክ ሄልዝ ነርስ በድምሩ 71 ባለሙያዎች ተቀጥረዉ ወደ ሴክተሩ እንዲቀላቀሉ ተደርጓል::

በበጀት አመቱም ከዚሁ ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ባለሙያ ሴክተሩን ለቆ ሄዷል:: ዘርዘር ባለመልኩ ለመግለጽ በድምሩ 69 /53 ወንድና 16 ሴት/ ባለሙያዎች ሴክተሩን ለቀዋል:: ሴክተሩን ለቀዉ ከሄዱትም 15 ሀኪሞች፣23 ነርሶች፣ 15 ላቦራቶሪ ቴክኒሻን፣4 ጤና መኮንን፣3 ጤና ተቆጣጣሪ፣4 ጤና ረዳት፣ 1 ፋርማሲስት 2 ድራጊስት፣ 1ዴንታል ቴራፒስትና አንድ ባዮሎጂስት ናቸዉ::

## የሙያ ስያሜ ምዝገባ

ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለክልሉ ጤና ቢሮ በተሰጠዉ ዉክልና መሰረት የክልሉ ጤና ቢሮ የመካከለኛ ጤና ባለሙያዎች ስያሜ ምዝገባ ከሀምሌ 1997 ጀምሮ ሲያካሂድ ቆይቷል:: በበጀት አመቱም 628 የተለያዩ የሙያ ዝግጁነት ያላቸዉ ጤና ባለሙያዎችን ተቀብሎ የሙያ ስያሜ ምዝገባ አካሂዷል:: ከነዚህም 354 ያህሉ የሙያ ምዝገባ ፈቃድ ተሰቷቸዋል::

# መድሃኒት አቅርቦትና አስተዳደር

ለክልሉ የተመደቡ መድሃኒቶችና የሕ/መ/መሣሪያዎች ከፌዴራል ጤና ጥበቃ በማምጣት ለዞኖችና ልዩ ወዳዎች እንዲከፋፈል ተደርጓል በዚህም መሠረት ፣

- በቤተሰብ ጤና ክብካቤ መምሪያ በኩል በእርዳታና በግዢ ከተለያዩ ምንጮች ብር 7,353,379 /ሰባት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሃምሣ ሦስት ሺህ ሦስት መቶ ሰባ ዘጠኝ ብር/ግምት ያላቸው መድሃኒቶችና የሕ/መ/መሣሪያዎች ገቢ ተደርገው ብር 5737,397አምስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሠላሳ ሰባት ሺህ ሦስት መቶ ዘጠና ሰባት ብር/ግምት ያላቸው ወደ ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች ተሰራጭተዋል::

- በኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዘርፍ በኩል ብር 3,844,100 (ሦስት ሚሊዮን ስምንት መቶ አርባ አራት ሺህ አንድ መቶ ብር ከአሥር ሣንቲም) ግምትያላቸው የተጓደኝ በሽታወች ማከሚያ አገልግሎት የሚውሉ መድሃኒቶች መጥተው 3,476,725 (/ሦስት ሚሊዮን አራትመቶ ሰባ ስድስት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ አምስት ብር)ግምት ያላቸው ወደ ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች ተሰራጭተዋል::

- ለ EOS ዘመቻ ሥራ አገለግሎት የሚውሉ የክትባትና ሌሎች ቁሳቁሶች 423,572 (አራት መቶ ሃያ ሦስት ሽህ አምስት መቶ ሰባ ሁለት ብር) ግምት ያላቸው መጥተው 3,914,926 (ሦስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አሥራ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ ስድስት ብር) ግምት ያላቸው እንዲሰራጩ ተደርጓል::

- ለጤና ኬላ አገልግሎት የሚውል 935,000. (ዘጠኝ መቶ ሠላሣ አምስት ሺህ ብር) ግምት ያላቸው የሕ/መ/መሣሪያዎች መጥተው ባሉን ጤና ኬላዎች ቁጥር እየተሠላ ጤና እንዲሠራጭ ተደርጓል::

- ለሠፈራ ጣቢያ አገልግሎት የሚውል መድሃኒቶችን ከፋርሚድ 1,000,000 (አንድ ሚሊዮን ብር) ግምት ያላቸው መድሃኒቶችንና የሕ/መ/መሣሪያዎችን ግዢ በመፈፀም 820,728.(ስምት መቶ ሃያ ሺህ ሰባት መቶ ሃያ ስምንት ብር) ግምት ያላቸው እንዲሠራጩ ተደርጓል::

- በሳንባ ነቀርሳና ሥጋደዌ ዘርፍ በኩልም እንደዚሁ 5,560,858.(አምስት ሚሊዮን አምስት መቶ ስልሣ ሺህ ስምንተ መቶ ሃምሣ ስምንት ብር ከሃምሣ ሣንትም) ግምት ያላቸው እንዲሁም፣ 10,245,764 (አሥር ሚሊዮን ሁለት መቶ አርባ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ስልሣ አራት ብር) ግምት ያላቸው መድኃኒቶችና የሕክምና መገልገያዎች መጥተው እንዲሰራጩ ተደርጓል::

- ለወባ ሕክመና እና መመሪመሪያ አገለግሎት የሚውለ 406,239 (አራት መቶ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሠላሣ ዘጠኝ ብር ከአሥራ ሁለት ሣንቲም) ግምት ያላቸው መሣሪያዎች

መጥተው 5,705,041 (አምስት ሚሊዮን ሰባት መቶ አምስት ሺህ አርባ አንድ ብር) ግምት ያላቸው እንዲሰራጩ ተደርጓል፡፡

- ለተጨማሪም በምግብ ለተጐዱ ህፃናት ሕክምና አገለግሎት የሚውለ 11,300. (አሥራ አንድ ሺህ ሦስት መቶ ብር) ግምት ያላቸው መድሃኒቶች መጥተው 50,000 (ሃምሣ ሺ ብር) ግምት ያላቸው መድኃኒቶች ተሰራጭተዋል፡፡
- በአጠቃላይ ከጤና ጥበቃ ሚ/ር ከግዥና ከእርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ገቢ የሆኑ 25,505,089 (ሃያ አምስት ሚሊዮን አምስት መቶ አምስት ሺ ሰማሚኒያ ዘጠኝ ብር) ግምት ያላቸው መድኃኒቶች ክትባቶች ሪኤጀንት እና የሕክ/መገ/መሣሪያዎች ሲሆኑ በበጀት አመቱም ከጠ ና ጥበቃ ሚ/ር ከግዥና ከእርዳታ ሰጭ ድርጅቶች የተገኙ ለዞኖችና ለልዩ ወረዳዎች ወጭ የሆኑ 34,648,086 (ሠላሳ አራት ሚሊዩን ስድስት መቶ አርባ ስምንት ሺ ሰማኒያ ስድስት ብር) ግምት ያላቸው መድኃኒቶች ክትባቶች ሪኤጀንቶች አና የህ/መገ/መሣሪያዎች ወጭ ተደርጓል፡፡

በክልሉ ያለዉን የመድሀኒት አቅርቦት በማሻሻል የሚሰጠዉን አገልግሎት ጥራትና የተገልጋዩን የመድሀኒት ፍላጎት ማርካት ይቻል ዘንድ እገዛ ያለዉ በተንከባላይ የበጀት ፊንድ የሚታገዝ ልዩ መድሀኒት ቤት በክለሉ ባሉ ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች ተቋቁመዉ አገልገሎት ሲሰጡ ያሉ መሆኑ ይታወቃል ፡፡ ይህም ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡ እስካሁንም በድምሩ ይህ አገልግሎት በ11 ሆስፒታሎችና123ጤና ጣቢያዎች እየተሰጠ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ በሰዉ ኃይል ልማት ፣በወረዳና ልዩ ወረዳዎች በቂ የመድሀኒት በጀት አለመያዝ ከፍተኛ ክፍተትና ጫና ማሳደር፣ ከዞንና ከወረዳ ጽ/ቤቶች መረጃዎች በወቅቱ አለመምጣት፣ የሲ/ሰ/ማሻሻያ ፕሮግራም ትግበራ ወጥነት ማጣትና የድህረ ምረቃነፕሮግራም የሚሰጡ ዩኒቨርሲቲዎች አስፈላጊዉን ማሰታወቂያና የጊዜ ገደብ አለማሳወቅ በአፈጻጸም ላይ ችግር ማሰከተላቸዉ ከሚጠቀሱት ናቸዉ፡፡

## የማኔጅመንትና የመረጃ አጠቃቀም፣ የድጋፋዊ ክትትል፣ግምገማና ምርምር

በዚህ የአገልግሎት ዘርፍ በበጀት አመቱ በቢሮዉ ዉስጥ ያለዉን የመረጃ መረብ በማጠናከር በመምሪያዎችና አገልግሎቶች መሰረታዊ የጤና አገልግሎት ሪፖርቶችንና መሰረታዊ መረጃዎችን ከአንድ ማዕከል ማግኘት የሚያስችል ስርዓት ለመዘርጋት የተያዘዉ እቅድ ተጀናዉኗል፡፡ በበጀት አመቱ ሊገነባ በእቅድ የታዘዉ የዳታ ቤዝ ህንጻም በእቅዱ መሰረት እየተከናወነ ይገናል፡፡ የፊዚካል ስራዉም 55 ፐርሰንት ተከናዉኗል፡፡ በመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ላይ የክህሎት ማዳበሪያ ስልጠ ና ለ300 ለባለሙያዎች ተሰቷል፡፡ በበጀት አመቱም ለማካሄድ የታቀደዉ አራት ድጋፋዊ ክትትል፣በተሳካ መልኩ ተካሂዷል፡፡ በተለያዩ የስራ መደራረቦች ሊካሄድ የታቀደዉ የአጋሮች የጋራ ምክክር መድረክ በበጀት አመቱ ማካሄድ አልተቻለም፡፡ ይሁንና የጤናዉ ሴክተር መማክርት ም/ቤት በየወሩ እየተገናኘ የሴክተሩን አፈጻጸም በጋራ የሚገመግምበት ስርአት ተዘርግቶ

የቅርብ ክትትል እየተደረገ ቆይቷል፡፡ ይህም መልካም የስራ ግንኙነትን ከመፍጠሩም በላይ የተሞክሮ ልዉዉጥ መድረክም ሆኖ ታይቷል፡፡ ይህም በቀጣዩ አመት ተጠናክሮ የሚካሄድ ይሆናል፡፡

በምርምር ረገድ በአመቱ አምስት ምርምሮችን ለማካሄድ የታቀደ ቢሆንም ሶስቱ ምርምሮች ተካሂደዋል፡፡ ሀለቱ በመካሄድ ላይ ናቸዉ፡፡ በዚህ የአግልግሎት ዘርፍ መከናወን ያከባቸዉ ተግባራት ሙሉ በሙሉ ያልተከናወኑ ቢሆንም የተቻለዉ ሁሉ ጥረት ተደርጓል፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ቢደት መሻሻል የሚገባቸዉ ጉዳዮችን እንዳሉ መጥቀስ አስፈላጊ በመሆ የሚከተሉት ክፍተቶች ታየተዋል፡፡በአጠቃላይ በጤናዉሴክተር አመራር የተሻለ የአፈጻጸም አቅጣጫዎች የተያዙ ቢሆንም ቼክ ሊስትን መሠረት የሚደረጉ ድጋፋዊ ክትትል እንደተፈለገው በየደረጃው አለመከናወን፣ የተሠሩትን ሥራዎች በጊዜ ለቅሞ መቀባበል የሚያስችል የመረጃ ፍሰት ክፍተት፣ያልተቀረፈ የጠ ባቂነት መንፈስ እና የቁጥቁጥ እቅዶች፣ የሴክተሮች ተቀናጅተው አለመሄድ፣የሥራ አመራር አቅም ማነስና በየደረጃው የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ጎልተው የታዩ የሴክተሩ ዓመቱ የበጀት ዓመቱ ጉድለቶችና ችግሮች ነበሩ፡፡

# የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዘርፍ

### ዘርፈብዙ ምላሽ

በበጀት ዓመቱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር፣ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ከተከናወኑ ተግባራት በግንባር ቀዳሚነት የሚጠቀስ ነው፡፡ በበጀት አመቱ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምክር ቤት 3ኛ መደበኛ ጉባኤ ከክልል ጀምሮ እስከ ወረዳና ቀበሌ ድረስ ባለው የአስተዳደር እርከን ተካሂዶ ጠ ቃሚ ውሳኔዎችን አስተላልፏል፡፡ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የድጋፍና እንክብካቤ ፈንድ እንዲቋቋም የተደረገ ሲሆን ከየካቲት 1998 ዓ.ም ጀምሮ ሁሉም የመንግሥት ሠራተኛ ከክልል እስከ ታችኛው እርከን ድረስ ከደመወዙ 0.5 በመቶ እንዲያዋጣ የጋራ መግባባት ላይ ተደርሶ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ለዚሁ ዓላማ የሚሆን መመሪያ ተዘጋጅቶ ለአስፈጻሚ አካላት እንዲደርስ ተደርጓል፡፡ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የእቅዶቻችን አካል የማድረግ ጉዳይ በሁሉም የሴክተር መስሪያ ቤቶች በመዋቅር ጭምር የሴቶችና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሜይንስትሪሚንግ ዩኒቲ በማቋቋም የተደገፈ ሲሆን እያንዳንዱ የመንግሥት መ/ቤት ከበጀት 2% ለዚሁ ሥራ እንዲያውል ተደርጓል፡፡

በበጀት አመቱ 65 ወጣቶችን በዋና አመቻችነትና 60 ጸረ ኤድስ ክበብ አባላትን የአቻ ለአቻ ስልጠና ለመስጠት የተቀመጠዉ ግብ ሙሉ በመሉ ተከናዉኗል፡፡

1700 የጤና ኤክስቴንሺን ባለሙያዎች በሚሰሩበት አካባቢ የማህበረሰብ ዉይይትን ማገዝ እንዲችሉ በአራት ጣቢያዎች የማህበረሰብ ዉይይት አመቻቶች ስልጠና ተሰቷል፡፡ በአጠቃላይ

በ1998 መጨረሻ በ1850 ቀበሌያት የማህበረሰብ ዉይይቶች የተካሄዱ ሲሆን 3700 የማህበረሰብ ዉይይት አመቻቶችም ሰልጥነዉ ተሰማርተዋል፡፡

በትምህርትና ቅስቀሳ ረገድም በበጀት አመቱ በርካታ ተግባራት ተከናዉነዋል፡፡ ከነዚህም የአለም ኤድስ ቀን በክልሉ በሁሉም አካባቢዎች እንዲከበር የተለያዩ መልዕክቶችን የያዙ በራሪ ጽሁፎችና ከ10 ሺህ በላይ ካኒቴራዎች ተዘጋጅተዉ ተሰራጭተዋል፡፡ ከደቡብ ኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያ ዘጠኝ የአየር ጊዜ በመግዛት የተለያዩ ዝግጅቶች ተላልፈዋል፡፡

ቀደም ሲል በህትመት ላይ የነበሩ ከ15 ሺህ በላይ መጽሄቶች፣ 9000 ፖስተሮች፣60 ሺህ በላይ በራሪ ጽሁፎች ታትመዉ እንዲሰራጩ ተደርጓል፡፡

በክልሉ የኤድስ መረጃ ማዕከልን ለማቋቋም በተደረገዉም ጥረት ምንም እንኳን ማዕከሉን የመገንባቱ ተግባር በበጀት አመቱ ባይጀመርም ለማዕከሉ መቋቋም አስተዋጽዎ ያላቸዉን የዉስጥ ማቴሪያሎችን ከፌዴራል የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ለማሰባሰብ በተደረገዉ ጥረት ማቴሪያሎቹን ማሰባሰብ ተችሏል፡፡ ሌሎችም ተጨማሪ ቁሳቁሶች ተገዝተዋል፡፡ የማዕከሉ ግንባታ በ1999 በጀት አመት የሚካሄድ ቢሆንም ማዕከሉን በጊዜያዊነት በኪራይ ቤት ለማስጀመር የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ተጠናቋል፡፡

### ድጋፍና እንክብካቤ

በቫይረሱ ሳቢያ ለተጎዱት ድጋፍና እንክብካቤ መስጠትን በተመለከተ በ1998 በጀት አመት በበጎ ፈቃደኛ ተንከባካቢዎች ለ 1259 የአልጋ ቁራኛ ለሆኑ በሽተኞች የቤት ለቤት እንክብካቤና ድጋፍ ፣ ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ 1050 ሰዎች በተለያዩ አካላት የምግብ፣ የህክምና እና የተለያዩ ድጋፎች የተሰጠ ሲሆን ከ 10 ሺህ በላይ ወላጅ ያጡና ተጋላጭ ህፃናት እንዲሁም አረጋውያን የተለያዩ ድጋፎችን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩትን ወይም ተጐጂዎችን እራሳቸውን መርዳት እንዲችሉ ለማድረግ 311 አባላት በገቢ ማስገኛ ፕሮግራም ታቅፈው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

### የህክምና አገልግሎት አቅርቦት

### በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የምክርና ምርመራ አገልግሎት/ቪሲቲ/

በ1998 በጀት አመት 50 ተጨማሪ የምክርና ምርመራ አገልግሎት የሚሰጡ ማዕከላትን በመክፈት ቁጥሩን በ1998 መጨረሻ ወደ 200 ለማሳደግ የታቀደ ሲሆን በበጀት አመቱ ተጨማሪ 50 ተቋማትን በማቋቋም በአሁኑ ወቅት በክልሉ 200 ጤና ጣቢያዎችና ሆስፒታሎች እንዲሁም በመያድና በተለያዩ ተቋማት ዉስጥ ባሉ የህክምና ማዕከላት የምክርና ምርመራ ማዕከላት ተቋቁመው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ በበጀት አመቱ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የምክርና ምርመራ አገልግሎትን ለ100ሺህ ተገልጋዮች ለመስጠት ታቅዶ አገልግሎቱን ለ75,562 ተገልጋዮችለመስጠት ተችሏል፡፡ አገልግሎቱን ካገኙት ዉስጥ 6817(3047ወንድ፣3770ሴት)

በደማቸዉ ቫይረሱ ተገኝቶባቸዋል፡፡ በፍቃደኝነት የምክርናየምርመራ አገልግሎትን ተጠቃሚነት በንጽጽር ስንመለከት በ1994 1,715 ሰዎች፣ በ1995 8,226 ተጠቃሚዎች፣ በ1996 መጨረሻ 26,380 እና በ1997 52 150 አግኝተዋል፡፡

ምንም እንኳን የምክርና ምርመራ አገልግሎት ተጠቃሚ ቁጥር መሻሻል እየታየበት ቢመስልም ከችግሩ ስፋት አንጻር በክልሉ ያሉ ተቋማት የሚሰጡት አገልግሎት በጣም ዉስን መሆኑን ያሉት መረጃዎች አመላካች ናቸዉ፡፡ ምንም እንካን ከዞን ዞንና ከወረዳ ወረዳ እንዲሁም ከጤና ድርጅት ጤና ድርጅት ልዩነት መኖሩ ቢታመንም በክልል ደረጃ በአማካይ ሲታይ አንድ ማእከል በቀን አገልግሎቱን የሚሰጠዉ ከአንድ ሰዉ ያልበለጠ መሆኑ በጣም ሊተኮርበትና ሊለወጥ የሚገባዉ ጉዳይ ነዉ፡፡



ሰንጠረዥ 17 : በፈቃደኝነት የኤች አይቪ ምክርና ምርመራ አገልግሎት ተጠቃሚነትና በደማቸዉ ቫይረሱ የተገኘባቸዉ ብዛት በዞንና ልዩ ወረዳ1998ዓም

| ተቁ | ዞን/ልዩወረዳ | በፈቃደኝነት የተመረመሩ ብዛት | በደማቸዉቫይረሱ የተገኘባቸዉ ብዛት | % በየአካባቢዉ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ቤ/ማጂ | 948 | 176 | 18.6% |
| 2 | ዳዉሮ | 643 | 33 | 5.1% |
| 3 | ጋሞጎፋ | 7221 | 644 | 8.9% |
| 4 | ጌዲኦ | 4258 | 361 | 8.5% |
| 5 | ጉራጌ | 14063 | 737 | 5.2% |
| 6 | ሀዲያ | 4021 | 285 | 7.1% |
| 7 | ካፋ | 1378 | 58 | 4.2% |
| 8 | ከም/ጠ | 2129 | 62 | 2.9% |
| 9 | ሸካ | 4319 | 153 | 3.5% |
| 10 | ሲዳማ | 7744 | 1452 | 18.8% |
| 11 | ስልጤ | 2745 | 157 | 5.7% |
| 12 | ደ/ኦሞ | 2302 | 211 | 9.2% |
| 13 | ወላይታ | 7447 | 892 | 12.0% |
| 14 | አላባ | 1177 | 73 | 6.2% |
| 15 | አማሮ | 956 | 7 | 0.7% |
| 16 | ባስኬቶ | 0 | 0 | 0 |
| 17 | ቡርጂ | 189 | 7 | 3.7% |
| 18 | ዲራሼ | 700 | 15 | 2.1% |
| 19 | ኮንሶ | 382 | 57 | 14.9% |
| 20 | ኮንታ | 370 | 11 | 3.0% |
| 21 | የም | 433 | 5 | 1.2% |
| 22 | አዋሳ አስተ | 11806 | 1330 | 11.3% |
| 23 | አዋሳሪፈራል ሆስፒ. | 331 | 91 | 27.5% |
| | ክልል | 75562 | 6817 | 9.0% |

ሰንጠረዥ18 : በፈቃደኝነት የኤችአይቪ ምክርና ምርመራ ተጠቃሚነት በዞንና በልዩ ወረዳ 1998ዓም

| ተቁ | ዞን/ልዩወረዳ | በፈቃደኝነት የተመረመሩ ብዛት | % ከክልሉ ጠቅላላ ተጠቃሚዎችአንጻር |
|---|---|---|---|

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | ቤ/ማጂ | 948 | 1.25% |
| 2 | ዳዉሮ | 643 | 0.85% |
| 3 | ጋሞጎፋ | 7221 | 9.56% |
| 4 | ጌዲኦ | 4258 | 5.64 |
| 5 | ጉራጌ | 14063 | 18.61 |
| 6 | ሀዲያ | 4021 | 5.32 |
| 7 | ካፋ | 1378 | 1.82 |
| 8 | ከም/ጠ | 2129 | 2.82 |
| 9 | ሸካ | 4319 | 5.72 |
| 10 | ሲዳማ | 7744 | 10.25 |
| 11 | ስልጤ | 2745 | 3.63 |
| 12 | ደ/ኦሞ | 2302 | 3.05 |
| 13 | ወላይታ | 7447 | 9.86 |
| 14 | አላባ | 1177 | 1.56 |
| 15 | አማሮ | 956 | 1.27 |
| 16 | ባስኬቶ | 0 | 0.0 |
| 17 | ቡርጂ | 189 | 0.25 |
| 18 | ዲራሼ | 700 | 0.93 |
| 19 | ኮንሶ | 382 | 0.51 |
| 20 | ኮንታ | 370 | 0.49 |
| 21 | የም | 433 | 0.57 |
| 22 | አዋሳ አስተ | 11806 | 15.62 |
| 23 | አዋሳ ሪፈራል ሆስፒ | 331 | 0.44 |
| | **ክልል** | 75562 | 100% |

<u>ሰንጠረዥ 19 :</u>**በፈቃደኝነት የኤችአይቪ ምክርና ምርመራ ተጠቃሚነት በዞንና በልዩ ወረዳ 1998ዓም**

| ተቁ | ዞን/ልዩወረዳ | በፈቃደኝነት የተመረመሩ ብዛት | የቪሲቲ ማዕከላት ብዛት | በአማካይ በአንድ ቪሲቲ ማዕከል የተመረመሩ ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ቤ/ማጂ | 948 | 9 | 105 |
| 2 | ዳዉሮ | 643 | 4 | 161 |
| 3 | ጋሞጎፋ | 7221 | 18 | 401 |
| 4 | ጌዲኦ | 4258 | 10 | 426 |
| 5 | ጉራጌ | 14063 | 28 | 502 |
| 6 | ሀዲያ | 4021 | 19 | 212 |
| 7 | ካፋ | 1378 | 11 | 125 |
| 8 | ከም/ጠ | 2129 | 9 | 237 |
| 9 | ሸካ | 4319 | 4 | 1,080 |
| 10 | ሲዳማ | 7744 | 29 | 267 |
| 11 | ስልጤ | 2745 | 12 | 229 |
| 12 | ደ/ኦሞ | 2302 | 6 | 384 |
| 13 | ወላይታ | 7447 | 16 | 465 |
| 14 | አላባ | 1177 | 3 | 392 |
| 15 | አማሮ | 956 | 2 | 478 |
| 16 | ባስኬቶ | 0 | 1 | 0 |
| 17 | ቡርጂ | 189 | 1 | 189 |
| 18 | ዲራሼ | 700 | 2 | 350 |
| 19 | ኮንሶ | 382 | 2 | 191 |
| 20 | ኮንታ | 370 | 1 | 370 |
| 21 | የም | 433 | 1 | 433 |
| 22 | አዋሳ አስተ | 11806 | 8 | 1,476 |
| 23 | አዋሳሪፈራል ሆስፒ | 331 | 4 | 83 |
| | **ክልል** | 75562 | 200 | 378 |

**የጸረ ኤች አይቪ ህክምና አገልግሎት / ART/**

የፀረ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ህክምና አገልግሎት በሚመለከት አገልግሎቱን የሚሰጡ ተቋማትን ከሶስት ወደ አስር ለማሳደግ የታቀደ ሲሆን እቅዱም ሙሉ በሙሉ ተከናዉኗል:: በበጀት አመቱም መጨረሻ 10 ሆስፒታሎች አገልግሎቱን እየሰጡ ይገኛሉ :: በአሁኑ ወቅት በድምሩ 2528

ሰዎች ነፃ የፀረ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መድሃኒት በመጠቀም ላይ ናቸዉ፡፡ ቀደም ሲል በፈቃደኝነት የሚሰጥ የምክርና ምርመራ አገልግሎት ተጠቃሚ ቁጥር መሻሻል ቢታይበትም አገልግሎቱን ማግኘት ከሚገባቸዉ ተገልጋዮች አንጻር ቁጥሩ ዝቅተኛ ነዉ ያልነዉ ቁልፍ ጉዳይ ለጸረ ኤች አይ ቪ ህክምናም በተመሳሳይ መልኩ መከሰት የምንሰጠዉ አገልግሎት ጉድለቱን ለይተን በማያት ማሻሻል እንዳለብን አመላካች በመሆኑ ልንፈትሸዉ ይገባናል፡፡ በአገር አቀፍ ደረጃ በ1997፣ 1998 እና 1999 እስከ ጥር መጨረሻ ድረስ ማከናወን ካለብን 12372 ተገልጋይ ዉስጥ ባለፉት ሁለት አመታት ያስመዘገብነዉ 2528 ተጠቃሚ ቁጥር በጣም ዝቅተኛ ነዉ፡፡ በዚህ አገልግሎት ዘርፍ እያጋጠሙካሉት ችግሮች ቀዳሚዎቹ የሰለጠኑ ባከሙያዎች እጥረትና የሰለጠኑትም ቢሆኑ የስራ ቦታ መልቀቅ፣ የሪኤጀንቶችና የሲዲ ፎር ማሺን እጥረትና በዚሁ ሳቢያ የአገልግሎቶች መቆራረጥ፣አድሎና መገለል፣ የተሰሩ ስራዎች በተሟላ መልኩ አለመቅረብና የሪፓርቶች መዘግየት፣ በመከላከሉና በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ያለዉ ቅንጅት ደካማ መሆን፣ የማህበረሰብ ዉይይት መዳከም፣ ዝቅተኛ የአገልግሎት ተጠቃሚነት እንዲሁም ለዘርፉ የሚቀርቡ በጀቶችን በወቅቱ ተጠቅሞ አለማወራረድ በቀዳሚነት ከሚጠቀሱት ናቸዉ፡፡ እስከ ሰኔ 30 1998 ድረስ በክልሉ እየተሰጠ ያለዉን የቅድመ ጸረ ኤች አይቪ ህክምናና የጸረ ኤች አይ ቪ ህክምና አገልግሎት አቅርቦት በተመለከተ አገልግሎቱን የሚሰጡትን ማዕከላት ባማከለ መልኩ - እንደሚከተለዉ ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡

| | On-ART | | | |
|---|---|---|---|---|
| **ART sites** | Childrens <14 years | Males >14years | Females >14 years | Total |
| Yirgalem hospital | 31 | 487 | 512 | 1030 |
| A/Minch hospital | 7 | 268 | 249 | 524 |
| Sodo hospital | 7 | 140 | 138 | 285 |
| Mizan hosp. | 7 | 73 | 82 | 162 |
| Hossaena hosp. | 3 | 31 | 58 | 92 |
| Dilla hosp. | 4 | 56 | 62 | 122 |
| Butajira hosp. | 1 | 36 | 56 | 93 |
| Jinka hosp. | 0 | 35 | 37 | 72 |
| Attat hosp. | 2 | 45 | 63 | 110 |
| Chench hosp | 0 | 17 | 21 | 38 |
| Total | 62 | 1188 | 1278 | 2528 |

| ART sites | non-ART | | | |
|---|---|---|---|---|
| | Childrens <14years | Males >14years | Females >14 years | Total |
| Yirgalem hospital | 61 | 649 | 779 | 1489 |
| A/Minch hospital | 21 | 490 | 542 | 1053 |
| Sodo hospital | 32 | 255 | 321 | 608 |
| Mizan hosp. | 13 | 104 | 135 | 252 |
| Hossaena hosp. | 20 | 92 | 179 | 291 |
| Dilla hosp. | 12 | 119 | 150 | 281 |
| Butajira hosp. | 7 | 75 | 127 | 209 |
| Jinka hosp. | 5 | 82 | 88 | 175 |
| Attat hosp. | 13 | 82 | 131 | 226 |
| Chench hosp | 3 | 33 | 41 | 77 |
| Total | 187 | 1981 | 2493 | 4661 |

| Grand total(non-ART & ART) care & support | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **ART sites** | Childrens <14years | Males >14years | Females >14 years | Total |
| Yirgalem hospital | 92 | 1136 | 1291 | 2519 |
| A/Minch hospital | 28 | 758 | 791 | 1577 |
| Sodo hospital | 39 | 395 | 459 | 893 |
| Mizan hosp. | 20 | 177 | 217 | 414 |
| Hossaena hosp. | 23 | 123 | 237 | 383 |
| Dilla hosp. | 16 | 175 | 212 | 403 |
| Butajira hosp. | 8 | 111 | 183 | 302 |
| Jinka hosp. | 5 | 117 | 125 | 247 |
| Attat hosp. | 15 | 127 | 194 | 336 |
| Chench hosp | 3 | 50 | 62 | 115 |
| Total | 249 | 3169 | 3771 | 7189 |

**ኤች አይ ቪ ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የመከላከል ህክምና አገልግሎት / PMTCT/**

ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ ይቻል ዘንድ የመከላከል ህክምና አገልግሎት በክልላችንም አየተሰጠ ይገኛል። በበጀት አመቱም ይህን አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ቋማትን ቁጥር በ1997 ከደረስንበት 11 ወደ 45 ለማሳደግ ታቅዶ በበጀት አመቱ አገልግሎቱን የሚሰጡ ተቋማት ቁጥር ወደ 32 ማሳደግ ተችሏል። እስከ በጀት አመቱ መጠረሻ በድምሩ በነዚህ ተቋማት

አማካኝነት  ለቅድመ ወሊድ ክትትል ከመጡ 44410  እናቶች ዉስጥ ለ 10070 እናቶች የቅድመ ምርመራ  የምክር አገልግሎት፣ የቅድመ ምርመራ የምክር አገልግሎት ካገኙት ዉስጥ 8100 በፍቃደኝነት ተመርምረዋል:: ከነዚህም ዉስጥ 7722 (80%) ለድህረ ምርመራ የምክር አገልግሎት መተዋል፣ከነዚህም ዉስጥ 366(4.5%) በደማቸዉ ዉሰጥ ቫይረሱ ተገኝባቸዋል:: እስከበጀት አመቱ መጨረሻም 159 እናቶችና 134 ህጻናት መድህኒት ወስደዋል::

ኤች አይ ቪ ቫይረስ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ መከላከል ህክምና ክልላዊ ገጽታ ሰኔ 30 1998 ድረስ

| | |
|---|---|
| አገልፍገሎቱን የሚሰጡ ተቋማት ብዛት | 32 |
| በተቋማቱ የቅድመወሊድ ክትትል የሚያደርጉ እናቶች ብዛት | 44410 |
| ቅድመ ምርመራ ምክር የተደረገላቸዉ እናቶች | 10,070 |
| ኤች አይቪ ምርመራ ያደረጉ | 8100 |
| ከምርመራ በኋላ ለምክር አገልግሎት የተመለሱ/የተሰጣቸዉ | 7,722( 80%) |
| ከተመረመሩት በደማቸዉ ቫይረሱ የተገኘባቸዉ | 366(4.5%) |
| መድህኒት የወሰዱ እናቶች | 159 |
| መድህኒት የወሰዱ ህጻናት | 134 |

ሰንጠረዥ20: Distribution of suspected and confirmed AIDS cases reported by age and sex, 1998 EFY

| Age | Suspected AIDS cases | | | AIDS cases | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | Male | Female | Total | Male | Female | Total | % |
| 0-4 | 37 | 31 | 68 | 18 | 10 | 28 | 2.8% |
| 5-14 | 42 | 76 | 118 | 16 | 18 | 34 | 3.4% |
| 15-19 | 49 | 99 | 148 | 3 | 20 | 23 | 2.3% |
| 20-24 | 117 | 146 | 263 | 29 | 90 | 119 | 11.9% |
| 25-29 | 171 | 231 | 402 | 81 | 128 | 209 | 20.8% |
| 30-34 | 190 | 190 | 380 | 95 | 114 | 209 | 20.8% |
| 35-39 | 171 | 119 | 290 | 101 | 82 | 183 | 18.2 |
| 40-44 | 114 | 54 | 168 | 59 | 25 | 84 | 8.4% |
| 45-49 | 69 | 38 | 107 | 35 | 23 | 58 | 5.8% |
| 50+ | 93 | 47 | 140 | 34 | 22 | 56 | 5.6% |
| Total | 1053 | 1031 | 2084 | 471 | 532 | 1003 | 100 |

Positivecases:  Married=482, unmarried=213, widowed=103, divorced=99

ሰንጠረዥ21: **HIVcare (non-ART & ART)-new and cumulative number of persons enrolled**

| ART sites | HIVcare (non-ART & ART)-new and cumulative number of persons enrolled | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | non-ART | | | | On-ART | | | | Grand total | | | |
| | Childrens <14years | Males >14years | Females >14 years | Total | Childrens <14years | Males >14years | Females >14 years | Total | Childrens <14years | Males >14years | Females >14 years | Total |
| Yirgalem hospital | 61 | 649 | 779 | 1489 | 31 | 487 | 512 | 1030 | 92 | 1136 | 1291 | 2519 |
| A/Minch hospital | 21 | 490 | 542 | 1053 | 7 | 268 | 249 | 524 | 28 | 758 | 791 | 1577 |
| Sodo hospital | 32 | 255 | 321 | 608 | 7 | 140 | 138 | 285 | 39 | 395 | 459 | 893 |
| Mizan hosp. | 13 | 104 | 135 | 252 | 7 | 73 | 82 | 162 | 20 | 177 | 217 | 414 |
| Hossaena hosp. | 20 | 92 | 179 | 291 | 3 | 31 | 58 | 92 | 23 | 123 | 237 | 383 |
| Dilla hosp. | 12 | 119 | 150 | 281 | 4 | 56 | 62 | 122 | 16 | 175 | 212 | 403 |
| Butajira hosp. | 7 | 75 | 127 | 209 | 1 | 36 | 56 | 93 | 8 | 111 | 183 | 302 |
| Jinka hosp. | 5 | 82 | 88 | 175 | 0 | 35 | 37 | 72 | 5 | 117 | 125 | 247 |
| Attat hosp. | 13 | 82 | 131 | 226 | 2 | 45 | 63 | 110 | 15 | 127 | 194 | 336 |
| Chench hosp | 3 | 33 | 41 | 77 | 0 | 17 | 21 | 38 | 3 | 50 | 62 | 115 |
| Total | 187 | 1981 | 2493 | 4661 | 62 | 1188 | 1278 | 2528 | 249 | 3169 | 3771 | 7189 |

ሰንጠረዥ22: **ART regimen at end of sene 1998 EFY,SNNPRS**

| ART regimen at end of sene 1998 EFY,SNNPRS | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ARTregimen** | year | Sex | A/minch | Chencha | Attat | Jinka | Sodo | Butajira | Dilla | Hossaena | Mizan | Yirgalem | Total |
| 1st. Line regimen | > 14 years | Male | 181 | 23 | 92 | 29 | 112 | 27 | 51 | 33 | 64 | 414 | 1026 |
| | | Female | 184 | 15 | 58 | 30 | 115 | 46 | 56 | 48 | 65 | 426 | 1043 |
| | | Total | 365 | 38 | 150 | 59 | 227 | 73 | 107 | 81 | 129 | 840 | 2069 |
| | <=14 years | Male | 549 | 0 | 2 | 0 | 4 | 0 | 1 | 1 | 4 | 14 | 575 |
| | | Female | 914 | 0 | 1 | 0 | 3 | 1 | 1 | 2 | 2 | 8 | 932 |
| | | Total | 1463 | 0 | 3 | 0 | 7 | 1 | 2 | 3 | 6 | 22 | 1507 |
| | | | | | | | | | | | | | 0 |
| | snb total | M | 730 | 23 | 94 | 29 | 116 | 27 | 52 | 34 | 68 | 428 | 1601 |
| | | F | 1098 | 15 | 59 | 30 | 118 | 47 | 57 | 50 | 67 | 434 | 1975 |
| | | T | 1828 | 38 | 153 | 59 | 234 | 74 | 109 | 84 | 135 | 862 | 3576 |
| | | | | | | | | | | | | | 0 |
| 2nd. Line regimen | > 14 years | Male | 2 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | | 2 |
| | | Female | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| | | Total | 2 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 |
| | <=14 years | Male | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| | | Female | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | | 0 |
| | | Total | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| | | | | | | | | | | | | | 0 |
| | sub. total | M | 2 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 |
| | | F | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| | | T | 2 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 |
| | | | | | | | | | | | | | 0 |
| | Grand total | Male | 732 | 23 | 94 | 29 | 116 | 27 | 52 | 34 | 68 | 428 | 1603 |
| | | Female | 1098 | 15 | 59 | 30 | 118 | 47 | 57 | 50 | 67 | 434 | 1975 |
| | | Total | 1830 | 38 | 153 | 59 | 234 | 74 | 109 | 84 | 135 | 862 | 3578 |

- **Regional HIV/AIDS Situation (in 2006)**
  - **Adult HIV Prevalence 3.1%**
    - **Female 3.5%**
    - **Male 2.7%**
      - **Urban 9.1%**
      - **Rural 2.6%**
  - **PLWHAs =235,937(under 15 yrs =17,136)**
  - **HIV positive pregnant women = 23,024**
  - **HIV positive births = 6,265**
  - **New HIV Infections = 35,619**
  - **New AIDS Cases = 19,523**
  - **Annual AIDS deaths = 17,931**
  - **AIDS cases newly in need of ART = 39,046**
  - **Orphans = 91,975**